## ጥናት 1 አስደሳች ዜና ጅማሬ (ማር.1፡ 4-11)

*መሠረተ አሳብ*

*መጥምቁ ዮሐንስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ታሪኩ እንደተገለፀው እንደ ነቢዩ ኤልያስ ዓይነት ልብስ ለበሰ፡፡(ቁጥር 6ን ከ2 ነገ. 1፡ 8 ጋር አመሳክር፡፡) በምድረ በዳ አንበጣና ማር መደበኛ ምግብ ነበሩ፡፡ የአንድን ሰው ጫማ ማውለቅ የዝቅተኛ አገልጋይ ወይም የባርያ ሥራ ነበር፡፡*

*ማሳሰቢያ*
*በቅንፍ ውስጥ የተቀመጠው ጥያቄ የሚመለሰው የቀደመው (ማለት ከቅንፉ በፊት ያለው ጥያቄ) በማንም ያልተመለሰ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡*

1. *አንድ ሰው የወጣትንቱን ዕድሜ ሁሉ በምድረ በዳ ለብቻው ቢያሳልፍ ምን ሊማር ይችላል? (ዮሐንስ በምድረ በዳ የነበረው የዕለትተዕለት ሕይወቱ እንዴት እንደነበረ አስብ፡፡)*
   - *በዚህ ምንባብ ነባራዊ ጊዜ ዮሐንስ ዕድሜው 30 ዓመት ያህል ሆኖት ነበር፡፡ በእርሱ ዕድሜ ክልል ያሉ ሌሎች የዘመኑ ወጣቶች የሚፈልጉትን ነገር ዮሐንስ ለምን አልተከተለም?*
   - *ዮሐንስ አገልግሎቱን በኢየሩሳሌም በዋና ከተማዋ ለምን አልሰጠም?*
   - *የዮሐንስ ታዋቂነት ምስጢር ምንድን ነበር?*

2. *ሰዎች በዮሐንስ ጥምቀት መጠመቅ የፈለጉበትን የተለያዩ ምክንያቶችን አስብ (4-5)፡፡*
   - *ዮሐንስ ሊያጠምቃቸው ከመስማማቱ በፊት ሰዎቹ ኃጢአታቸውን በግልጽ መናዘዝ ለምን አስፈለጋቸው? (5)*
   - *ኃጢአትህን አስቀድመህ በግልጽ እንድትናዘዝ ብትጠየቅ ለመጠመቅ ትስማማለህ?*
   - *የዮሐንስ አገልግሎት ለኢየሱስ እንዴት መንገድ አዘጋጀ? (2-4) (ኢየሱስ የራሱን አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት የዮሐንስ አገልግሎት ለምን አስፈለገ?)*
3. *ኢየሱስ ወደ ልባችን እንዲገባ እንዴት ልባችንን ማዘጋጀት እንችላለን ? (3)*
   - *ኢየሱስ ወደ ሌሎች ሰዎች ሕይወት እንዲገባ እንዴት መንገድ ልናዘጋጅለት እንችላለን? (ለምሳሌ፡- ወደምንወደው ሰው ሕይወት ውስጥ እንዲገባ መንገዱን እንዴት እናመቻቻለን?)*
4. *ታዋቂነቱ ዮሐንስን ለምን አላኮራውም?*
   - *ዮሐንስ የሚመጣውን የመሢህ ጫማ ማሠሪያ ለመፍታት የሚገባ መሆኑን ለምን አልገመተም?*
5. *በዮሐንስ ጥምቀትና በኢየሱስ ጥምቀት (ማለትም የክርስቲያን ጥምቀት) መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ኢየሱስ ተከታዮቹን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃል ማለቱ ምን ማለት ነው (8)?*
   - *በዚህ ንባብ መሠረት ለደህንነት (ለመዳን) ጥምቀት ለምን አስፈለገ?*

6 *ኢየሱስ የሚናዘዘው አንዳች ኃጢአት ባይኖረውም እንኳን ለምን የንስሐ ጥምቀት ለመጠመቅ ፈለገ?*

7 *በኢየሱስ ጥምቀት ጊዜ ሥላሴ (እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ፣ መንፈስቅዱስ) የተገኘው እንዴት ነበር?*

- *እግዚአብሔር አባት ለልጁ ያለውን ፍቅር በኢየሱስ ጥምቀት ወቅት ለምን በቀጥታ ከሰማይ አስታወቀ? (11)*

8. *በዚህች ወቅት ሰማያዊ አባት ሲመለከትህ በቁጥር 11 ላይ የተጻፈውን ቃል ስለ አንተም መናገር ይችላል ብለህ ታስባለህን? ምክንያትህን ግለፅ፡፡*

**አስደሳች ዜናዎች፤**
በ11 ቁጥር ውስጥ ያሉት ቃላት እግዚአብሔር ለአብርሃም ያለውን ነገር ያስታዉሳሉ፡፡
«የምትወደው አንዱን ልጅህ ይስሐቅ ይዘህ ወደ ሞሪያ ተራራ ሂድና ሰዋው፡፡» (ዘፍ.22፡2)
የኢየሱስ ጥምቀት ወደ መስቀሉ በሚያደርገው ጉዞ የመጀመሪያው እርምጃ ነው፡፡

## ጥናት 2. ጤናማዋ ነፍስ በጤናማው ሰውነት ውስጥ (ማር. 2፡ 1-12)

*መሠረተ አሳብ*

በኢየሱስ ዘመን ቤቶች ጠፍጣፋ ጣሪያዎች ነበሩአቸው፡፡ በአሸዋማ አፈር (ኖራ) እና በሸክላ ጡቦች የተሠሩ ነበሩ፡፡ በመሆኑም በዘመናችን ካሉት የቤት ጣሪያዎች ይልቅ ለመክፈትም ሆነ ለመስበር ቀላል ነበሩ፡፡ ከውጪ በቀጥታ ወደ ጣሪያው የሚያደርሱ መረማመጃዎች (መሰላል) ይሰራላቸው ነበር፡፡ የአንድ ሰው ሽባ መሆን አብዛኛውን ጊዜ የሚፈጠረው የጭንቅላት ውስጥ መድማት በመካከለኛ ዕድሜ ወይም ዘገይቶ በሚከሰትበት ጊዜ ነው ፡፡ በዚህ ክፍል «የሰው ልጅ» ማለት ኢየሱስ ራሱ ነው፡፡

1. የአንድን ሽባ ሰው የዕለትተዕለት ሕይወት አስብ፡፡ እንዴት ያለ አስቸጋሪ ሁኔታ መጋፈጥ አለበት? ምን ዓይነት እንክብካቤ እንዲደረግለት ያስፈልገዋል? ከበሽታው የተነሣ ከሰው ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት ሊለወጥ እንደቻለ አስብ፡፡ የወደፊት ሕይወቱ እቅድና ሕልም ምን ሊመስል እንደሚችል አስብ፡፡ የዚህ ሰው የመኖር ትርጉም ምንድን ነው?
    - ለዚህ ሽባ ሰው እንክብካቤ የሚያደርግ ሰው የየዕለቱን ሁኔታ ምን ሊመሰል እንደሚችል አስብ፡፡ ሕይወቱ ምን ይመስል ይሆን?

2. በቁጥር 4 ላይ ይህ ሰው ኃጢአተኛ እንደነበር ግልጽ እየሆነ የመጣ ይመሰላል፡፡ ለመሆኑ አንድ ሰው ለራሱ መንቀሳቀስ በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ምን ዓይነት ኃጢአት ይሠራ ይሆን?
    - ተወያዩበት! በሽታ ሰውን የተሻለ ሰው ወይም ክፉ ሰው ሊያደርግ ይችላል?

3. ሰውዬውን የተሸከሙ ሰዎች እነማን ነበሩ? በተለያዩ አማራጮች ላይ ተወያዩ!
    - በቁጥር 3-4 በተመለከተው ቃል መሠረት ሰዎቹን ደፋሮች ያደረገው ነገር ምንድነው ?
    - እነዚያ ሰዎች ሰውዬውን በኢየሱስ ዘንድ ለማቅረብ ከቤት ጀምሮ ደረጃ በደረጃ ምን ማድረግ እንደነበረባቸው አንድ በአንድ አስብ! (ቀላሉ ሥራ ምን ነበር? አስቸጋሪውስ?)

4. ሰዎቹ ሽባው ዘመዳቸው ይፈወስ ዘንድ ወደ ኢየሱስ አመጡት፡፡ ኢየሱስ በሽተኛውን ከመፈወሱ በፊት አስቀድሞ ለኃጢአቱ ለምን ይቅርታ አደረገ? (ኢየሱስ ለምን በዚህ መንገድ ሠራ)?
    - ለሽባው ሰውዬ የኃጢአት ሥርየት ምን ትርጉም አለው?

5. የከፋ ችግርህን ወደ ኢየሱስ ስታቀርብ ለችግርህ መፍትሔ ከመስጠት ፈንታ «ልጄ ሆይ ኃጢአትህ ተሠረየልህ» ቢልህ ታዝናለህ ወይስ ትደሰታለህ?
    - መልካም ሕሊና ኖሮህ ችግርህ መፍትሔ ባያገኝ ነው ወይስ ሕሊናህ በሽተኛ ሆኖ ለችግርህ ግን መፍትሄ ብታገኝ ትመርጣለህ ? ኃጢአቱ ይቅር በተባለለት ጊዜ ሽባው ሰውዬ ልቡ ሲበራ ስለ በሽታው ያለው አመለካከት እንዴት የተለወጠ ይመስልሃል?

6. በቁጥር 5 ላይ ኢየሱስ ወደ ማን ኃጢአት እያመለከተ ነው? የዓረፍተ ነገሩን አወቃቀር ዝግ ብለህ ተመልከት፡፡
    - በምን ወቅት ነው ሽባው ሰውዬ በኢየሱስ ማመን የጀመረው?

7. ኢየሱስ በቁጥር 9 ላይ ላነሳው ጥያቄ መልስ ስጥ፡፡ ሰውዬውን ለመፈወስ ኢየሱስ ምን አይነት ዋጋ አስከፈለው? (የሰውዬውን ኃጢአት ይቅር ለማለት ምን ዓይነት ዋጋ አስከፈለው?)

8. ይህ ጥቅስ ስለ እምነት ብቻ ሳይሆን ስለ አለማመንም ይናገራል፡፡ የሕግ አስተማሪዎች ኢየሱስ ኃጢአት ይቅር ለማለት እንደሚችል ለምን ለማመን አልፈለጉም?

9. የምንወዳቸው ወገኖች ሆነው በራሳቸው ወደ የሱስ ለመምጣት ግን መወሰን የማችሉትን ወይም መምጣት የማይፈልጉትን እንዴት «ተሸክመናቸው» ወደ ኢየሱስ ልናመጣቸው እንችላለን? (ኢየሱስን የት ለማግኘት ይችላሉ?)

10. ኢየሱስ ወደዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የመራህ «ልጄ ሆይ ኃጢአትህ ተሠርዮልሃል» ሊልህ ፈልጎ ነው፡፡ አሁን ባለህበት ሁኔታ ውስጥ ይህ ቃል ምን ትርጉም ይሰጥሃል?

## ጥናት 3. ለኢየሱስ የተቀመጠ ማሰናከያ (ማር. 3:1-6)

*መሠረተ አሳብ*

ስለ ሰንበት በኢየሱስና በተቃዋሚዎቹ መካከል የተደረገው የመጀመሪያው ክርክር በማር.2:23-28 ውስጥ ተገልፆአል:: የአሁኑ ሁለተኛው ነው:: ትንሹን የሰንበት ሕግ መጠበቅ እንደ ፈሪሳውያን አሳብ የመሢህ መምጣትና የሰው ደህንነት ምክንያት ነው::

1. የሰለለው እጅ በዚህ ሰውዬ የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ያሳድራል? (ሥራውን፣ ገቢውን፣ ቤተሰቡን እና ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውንም ግንኙነት በሚመለከትስ የሚኖረው ተፅዕኖ ምንድነው?) በዘመናችን በአንድ እጅ ብቻ ለሚገለገል ሰው ምን ዓይነት ሥራ ይገኝለታል?
    - በቁጥር 5 ላይ የዚህ ሰውዬ እጅ ቀድሞ ደህና እንደነበረ እንረዳለን:: የዚህ ሰውዬ እጅ እንዲሰልል ያደረገው ነገር ምን እንደነበረ ታስባለህ? ምናልባት በአደጋ ይሆን?
    - ከዚህ ንባብ ክፍል ስለዚህ ሰውዬ ጠባይ የነካህ ምን ዓይነት ነገር አገኘህ/ሽ?
2. በዚያች ጧት ምኩራቡ አካባቢ ያለው (ሁኔታ) «መንፈስ» ምን ይመስል ነበር?
    - ሰውዬው ወደ ምኩራብ የመጣው ለመፈወስ እንዳልሆነ ከጥቅሱ ለመረዳት እንችላለን? ለምን ነበር የመጣው?
    - ይህ ሰውዬ ኢየሱስን ለምን እርዳታ አልጠየቀውም?
    - የዚህ ሰውዬና የፈሪሳውያን በዚያ ሰንበት ወደ ምኩራብ መምጣታቸው በስተጀርባ ያለው ሀሳብ ምን እንደሆነ አመዛዝን::
3. ፈሪሳውያን ስለ ኢየሱስ ያሰቡት ነገር ስህተት እንደሆነ ፊትለፊት ለኢየሱስ በመናገር ለምን አልከሰሱትም?
    - እጁ ስለ ሰለለው ሰውዬ ፈሪሳውያን ምን ያስቡ ነበር?

4. ኢየሱስ ሰውዬው በነበረበት ቦታ ከመፈወስ ፈንታ በሁሉ ፊት ተነስቶ እንዲቆም ለምን አዘዘ?
    - ሰውዬው በማንኛውም ሰው ትዕዛዝ ተነሥቶ ይቆማል ብለህ ትገምታለህ?

5. በቁጥር 4 ውስጥ ኢየሱስ በብልሃት የራሱን ዓላማና የተቃዋሚዎቹን ሃሳብ ይገልፃል:: ኢየሱስ ጠበቅ ባለ አነጋገር «ሕይወትን ማዳን ወይም መግደል» ሲል ምን ማለቱ ነው? (የፈሪሳውያን ባህሪ (ሁኔታ) ይህን ሰው ምን ያህል የገደለ ይመስላል? ኢየሱስ የሰውዬውን ሕይወት እንዴት አዳነ?)

6. ኢየሱስ እንደሚቆጣ አራቱ ወንጌሎች አልፎ አልፎ ይጠቁማሉ:: በዚህ ንባብ ነባራዊ ሁኔታ ኢየሱስ ለምን ተቆጣ? ለምንስ አዘነ ? (5)

7. ሰውዬው እጁን እንዲዘረጋ በተነገረው ጊዜ ስለ ኢየሱስ ምን ዓይነት እምነት ነበረው?
    - ኢየሱስ ስለ እምነት ምን ዓይነት ተመሣሣይ እርምጃ ዛሬ ካንተ ይጠብቃል?

8. ከኢየሱስ ንግግርና ሥራዎች ፈሪሳውያንን ያስቆጣቸውና ሊገሉትም እንዲያሴሩ ያደረጋቸው ነገር ምንድነው ?
    - በዚህ ክስተት ላይ እንደተመለከተው ፈሪሳውያን በእግዚአብሔር ላይ ካላቸው እምነት ስህተት የሆነው ነገር ምንድነው?

9. ኢየሱስ የራሱን ሕይወት ለአደጋ እስኪያጋልጥ ድረስ የዚህ ሰውዬ መፈወስ ለምን ጠቃሚ ሆኖ ተገኘ (4)?
    - ኢየሱስ ሰዎችን ቢረዳና ቢያድንም እንኳን ለምን ተገደለ (4)?

**አስደሳች ዜናዎች፤**

ስለ ሰንበት ጉዳይ ኢየሱስ ባስተማረውና ፈሪሳውያን በሚያስተምሩት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ:: እንደ ፈሪሳውያን ትምህርት ሰው ለመዳን ሕግን ሙሉ በሙሉ መጠበቅ አለበት:: ሰንበትን መቀደስ ለፈሪሳውያን የሰው ልጆች ለመዳን መፈፀም ያለበት ሕግ ተደርጎ ይቆጠራል:: ለኢየሱስ ግን የወንጌል መልክ ያለው ሲሆን እግዚአብሔር በኃጢአታቸው ስርየት (ይቅርታ) ለሚያምኑቱ ቅዱሳን የሚሰጠው ዕረፍት ማለት ነው:: (ዕብ. 4: 9-10)

## ጥናት 4. በማዕበሉ መካከል ( ማር. 4፡ 35-41)

**መሠረተ አሳብ**

በደቀ መዛሙርቱ መካከል አራት (4) የዓሣ በማጥመድ የታወቁ ባለሙያዎች ነበሩ፡፡ እነዚህም ሰዎች ልክ እንደ እጃቸው መዳፍ የገሊላን ባሕር ያውቁ ነበር፡፡

1. የገሊላ ባህር ስፋት መጠን 20 x 12 ኪሎሜትር ነው፡፡ እንደዚህ ያለውን ባህር ለመሻገር በግምት ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?
    - አንድ ሰው ይህንን ባሕር በሌሊት እንድትሻገር ቢጠይቅህ ምን ታስባለህ?
    - ኢየሱስ በዚያች ሰዓት ባሕሩን እንዲሻገሩ ደቀ መዛሙርትን ባዘዘ ጊዜ ለምን አልተከራከሩም?
2. በማዕበል በሚናወጥ ጀልባ ውስጥ ሰውን የሚያስተኛ ነገር ይኖራል ብለህ ታስባለህ? የተለያዩ ማብራሪያዎችን ለመስጠት አስብ፡፡ (ይህ ሁኔታ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነትና ከሞቱ ጋር ስላለው ግንኙነት ምን ይገልፃል)?

3. ጀልባው እንዳይሰምጥ ለማድረግ ደቀ መዛሙርቱ ምን ዓይነት እርምጃ ወስደዋል?
    - ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ለምን በእግዚአብሔር ኃይል አላመኑም?
4. አንተና ወዳጅህ ልትሰጥሙ የደረሳችሁበት ጊዜ ገጥሞህ ኢየሱስ የተኛና ጥቂትም እንዳልተጠነቀቀላችሁ መስሎ የተሰማህ ጊዜ ነበርን (38)? ሁኔታውን ለጓደኞችህ አካፍል፡፡
    - በእርግጥ ቁጥር 38 ጸሎት ነው፡፡ ከዚህ ቁጥር ስለ ጸሎት ምን እንማራለን?

5. የተመኙትን እርዳታ ባገኙ ጊዜ ደቀ መዛሙርት ለምን ተደነቁ?
    - እስኪ ችግር በቅርቡ ገጥሞሃል? ምን ነበር? በገጠመህ ሁኔታ ምክኒያት ከደቀ መዛሙርት ጋር የምትመሣሰልበትና የምትለይበት ሁኔታ ምንድነው?

6. በችግራችን ውስጥ ምን ዓይነት እርዳታ ከኢየሱስ እንሻለን?

7. ንፋስና ማዕበል በእርግጥ ለኢየሱስ መታዘዙን ማመን ላንተ ቀላል ነው ወይስ አስቸጋሪ ነው? (39) በሁለቱም አነፃር ምክንያቶችህን ግለፅ፡፡

    - በዚህ ጊዜ ኢየሱስ አንተን ባጋጠመህ ማዕበል መካከል ቆሞ «ዝም በል ፀጥ በል» ይላል፡፡ ባለህበት ሁኔታ ውስጥ ቃላቶቹ ምን ትርጉም ይሰጡሃል፡፡

8. ደቀመዛሙት ከኢየሱስ አፍ በቁጥር 40 ላይ የተጠቀሰውን ቃል በሰሙ ጊዜ ምን ተሰማቸው?
    - ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረውን ቃል ለአንተ ቢናገር ምላሽህ እንዴት ይሆን ነበር? (40)

9. በዚህ ክፍል ደቀመዛሙርቱ የፈሩአቸው ሁለት ዓይነት ፍርሃቶች (ማለትም በማዕበሉ ምክኒያት የፈሩትንና ኋላም ኢየሱስ ማዕበሉን በማስቆሙ የተሰማቸውን ልዩ ፍርሃት) መካከል ያለው ልዩነት አሰረዳ (40-41)፡፡

10. በዚህ ክፍል መሰረት ኢየሱስ እምነት የሌላቸውን ሰዎቸ ሲረዳ እናያለን፡፡ ለምን?

    - በዚህ ሁኔታ ውስጥ የደቀ መዛሙርቱ እምነት እንዴት ተለወጠ?
    - አሁን እያለፍክበት ባለው ችግር ውስጥ እምነትህ እንዲለወጥ ምን ያህል ትወዳለህ?

**አስደሳች ዜናዎች፤**

በዚህ ክፍል ደቀ መዛሙርት ከመስጠም አደጋ ተርፈዋል ኢየሱስ ግን ከዚህም በሚበልጥና አስፈሪ ባሕር ሰምጧል፡፡ በመስቀል ላይ መቸንከር በባህር ውስጥ ሰጥሞና ታፍኖ ከመሞት ጋር እኩል ነው ወይም ይብሳል ፡፡ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን መሪው መዝ.69፡ 1-2 እና 14-15 ያንብብ፡፡ ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ስቃይ ከሚገልጡ መዝሙሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ በእሳት ባሕር ከመስጠም ሊያድነን ኢየሱስ የከፈለው ዋጋ ነው፡፡ (ራዕ.20፡14)

## ጥናት 5. ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ (ማር. 5፡ 1-20)

*መሠረተ አሳብ*

በዚህ ጥቅስ ውስጥ የሚገኘው ሰው ምናልባት ጣዖት የሚያመልክ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ይህ ሰው እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በሚበዙበት በገሊላ ባህር በስተ ምስራቅ በኩል ስለሚኖር ነው። በዚያ የሚኖሩ ጣዖት አምላኪዎች አሳማን በማርባት የሚኖሩ ሲሆን፡ ይኽ ደግሞ ለአይሁዶች የማይፈቀድ ነገር ነው። ርኩስ መንፈስ አብዛኛውን ጊዜ ጣኦት የሚያመልከውን ሰው ይይዛል። በክፍሉ የተጠቀሰው ሌጌዎን የሚለው ቃል 6000 ወታደሮችን ከሚይዝ የሮማውያን ሠራዊት ጭፍራ ጋር እኩል ነበር።

1. በርኩስ መንፈስ የተያዘው ሰውዬ ቤተሰብ ነበረው (19)። ቤተሰቡ ሰውዬውን ከዚህ አሰቃቂ ዕድል ለማዳን ምን ዓይነት ሙከራ አድርገው ነበር?
   - በዚህ አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ለሚስቱ ለልጆቹና ለወላጆቹ በጣም ከባዱ ነገር ምንድን ነው? (3-5)
   - በዚህ ጥቅስ ውስጥ ከሚገኘው ሰውዬ ሁኔታ ጋር የሚመሳሰሉ በዘመናችን ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች የሚባሉት ምን ዓይነት ነገሮች ናቸው?

2. በቁጥር 3-7 ካሉት ነገሮች ውስጥ ሰውዬው በፈቃዱ ምን አደረገ? በርኩስ መንፈሱ እንዲያደርግ የተገደደውስ ነገር ምንድን ነው።
   - ይህ ሰውዬ ከኢየሱስ የፈለገው ነገር ምንድን ነው? (6-7) በሰውዬው ጠባይ ውስጥ ምን ዓይነት ተቃርኖዎች ታያለህ?
3. ሰውዬው ስለ ኢየሱስ አስቀድሞ ምን ያውቅ ነበር? ይህንንስ መረጃ ( ወሬ) ከየት አገኘ (7)?

4. የ6000 ርኩሳን መናፍስት በአንድ ሰው ውስጥ መግባት በምን ምክንያት ይከሰት ይሆን? (9)
   - በኢየሱስና በርኩስ መናፍት መካከል የተደረገው ንግግር በማይታየው ዓለም ስላለው የኃይል አወቃቀር ምን ያሳየናል (8-13)?
   - ርኩሳን መናፍስት ለማድረግ የጠየቁትን እንዲያደርጉ ኢየሱስ ለምን ፈቀደላቸው?
   - ምናልባት በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን አባላት ውስጥ መናፍስትን፣ ምትሃትና ጨለማን የሚፈሩ ይኖሩ ይሆናል። ለእንዲህ ዓይነት ሰው ይህ ክፍል ምን ምክር ይሰጠዋል?
5. የጌርሴኖን ሰዎች ጎረቤታቸው በመዳኑ ለምን አልተደሰቱም? (14-17)
   - በአሁኑ ጊዜ 2000 አሳማዎች ምን ያህል ዋጋ ያወጣሉ?
   - አንድን ሰው ለማዳን ብሎ ኢየሱስ ንብረትህን ሁሉ ቢያጠፋ ምን ታደርጋለህ?
6. በዚህ በዳነው ሰው ሕይወት ውስጥ ስንት ነገሮች ተለወጡ?
   - ይህ ሰው ኢየሱስን ካገኘ በኋላ በዋሻ ውስጥ ስላሳለፋቸው ዓመታት ምን እንደ አሰበ ትገምታለህ? (ኢየሱስ የዚህን ሰውዬ ሕይወት ከዜሮ ወደ ትልቅ ደረጃ እንዴት ለወጠው?)
7. ኢየሱስ ይህ ሰው እንዲከተለው ለምን አልፈቀደለትም (18-19)?
   - አይሁዶች በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲያደርጉ ሳይፈቅድ ስለዚህ ተአምር እንዲናገር ኢየሱስ ይህንን ከአሕዛብ ወገን የሆነውን ሰው ለምን አዘዘ?
8. በቁጥር 19 ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ኢየሱስ ዛሬ ለሁላችን ይናገራል። በአሁኑ ሁኔታህ ውስጥ ምን ትርጉም ይሰጡሃል? (ለቤተሰብህ እንድትናገር ኢየሱስ የሚፈልገው ትልቁ ነገር ምንድን ነው?)
   - በዚህ ጥቅስ መሠረት ተስፋ አስቆራጭ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንዳለ አድርገህ ስለምታስበው ሰው ሰው እንዴት ትጠነቀቅለታለህ?
9. ኢየሱስ ከሰይጣን ጋር ያደረገውን ፍልሚያ አስር ለዜሮ አሸንፏል። ታዲያ በየቀራኒዮ በነበረው ክርክሩ ለምን ተሸነፈ?

**አስደሳች ዜናዎች፤**

የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን መሪው ኢሳ. 52:14 እና ኢሳ.53:3 ያንብብ። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከጌርሴኖን ሰው ጋር የሚመሳሰልበት ሁኔታ ነበረው። በዚያች ወቅት ርኩስ መናፍስት እንዲያሰቃዩት ተፈቀደላቸው። ይህም የሆነው ኢየሱስ በዚያች ወቅት በእግዚአብሔር ፊት የኃጢአታችንን ቅጣት (ክስ፣ ዕዳ) ስለተቀበለ ነው።

## ጥናት 6. እጅግ አስከፊ የሆነ ነገር ሲከሰት (ማር. 5፡ 21- 24 እና 35-43)

*መሠረተ አሳብ*

አብዛኛውን ጊዜ የምኩራብ አለቃ የሚመረጠው እጅግ ከተከበሩ የከተማዋ ሰዎች መካከል ነበር፡፡ ከያኢሮስ በስተቀር የምኩራብ አለቆች ሁሉ በወንጌል ውስጥ የኢየሱስ ተቃዋሚዎች እንደነበሩ ተመልክቷል፡፡ ይህ ሰው ይህችን ልጅ ብቻ ነበረው (ሉቃስ 5:42)፡፡

1. ለብዙ ጊዜ ሲጠባበቋት የነበሯት ይህች ልጅ ከተወለደች በኋላ የዚህ አነስተኛ ቤተሰብ የየዕለት ሕይወት እንዴት ሊሆን እንደሚችል አስብ፡፡

2. ሕጻኒቱ ስትታመም በወላጆች ግንኙነት መካከል ምን ይከሰታል? ሊከሰቱ የሚችሉት የተለያዩ ነገሮችን አስብ፡፡
   - ልጅቷ ከታመመች በኋላ በያኢሮስና በእግዚአብሔር ግንኙነት መካከል ምን እንደሚከስት አስብ፡፡

3. ያኢሮስ እርሱ በሚኖርበት መንደር ታዋቂነት ከሌለው ሰው እርዳታ ለማግኘት ለምን ፈለገ?
   - ያኢሮስ ኢየሱስን እርዳታ ከጠየቀበት መንገድ ምን ልንማር እንችላለን? (22-23)

4. ከቤቱ መጥፎ ዜና ከሰማ በኋላ በያኢሮስ ልብ ውስጥ ምን ተሰማ (35)?
   - ከእንግዲህ ኢየሱስን ማስቸገር ምንም ጥቅም የለውም የሚል ስሜት ተሰምቶህ ያውቃል? ይህ መቼ ነው የተከሰተው?

5. እጅግ የከፋ ነገር ቢከሰትም እንኳ ኢየሱስ ያኢሮስን ለምን «አትፍራ» አለው (36)?
   - በምድር ላይ በጣም የሚያስፈራህ ነገር ምንድን ነው? (በልብህ ወይም በሃሳብ መልስ መስጠት ትችላለህ፡፡)
   - የከፋ ነገር ከደረሰብህ በኋላ ኢየሱስ «አትፍራ» ቢልህ ምን ታደርጋለህ (ትላለህ)?

6. ኢየሱስ ዛሬ «አትፍራ እመን እንጂ» ቢልህ አንተ ባለህበት ሁኔታ ውስጥ እነዚህ ቃላት ምን ትርጉም ይሰጡሃል?
   - ልጅቷ ከሞተችም በኋላ እንኳን ያኢሮስ ምን ሊያምን ችሎ ነበር?
   - ያኢሮስ በኢየሱስ ፈጽሞ ባያምን ኖሮ ምን ሊያደርግ ይችል ነበር?

7. የያኢሮስ ሚስት ባሏ ከቤት ርቆ በነበረነት ሁኔታ ልጇ ስትሞት በዓይኗ ተመለከተች፡፡ ኢየሱስና ባሏ ወደ ቤት በመጡ ጊዜ የአእምሮዋ ሁኔታ ምን እንደነበር ታስባለህ?
   - ኢየሱስ ወደ ኢያኢሮስ ቤት በደረሰ ጊዜ የቀብር ዝግጅት እየተደረገ ነበር፡፡ በቁጥር 39 ውስጥ በተጠቀሰው ቃል በኩል ኢየሱስ ለእንግዶቹ ምን መናገር ፈለገ?

8. ኢየሱስ ልጅቷን እንዴት ከሞት እንዳስነሣ በዝግታ አንብብ (41-43) ፡፡ ከተገለፀው ነገር ውስጥ በልዩ ሁኔታ የሚያስደንቅህ ምንድር ነው?

9. አገልግሎቱን በሕዝብ ዘንድ ታዋቂ ለማድረግ መልካም አጋጣሚ ቢሆንም እንኳን ኢየሱስ ስለ ተአምራቱ እንዳይናገሩ ለምን ጥብቅ ትዕዛዝ ለሰዎቹ ሰጠ?

10. ይህ ክስተት በልጅቷ ሕይወት ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ይኖረዋል? የወደፊት ኑሮዋ ላይ እንዴት ተፅዕኖ ይኖረዋል?
    - የወላጆችዋ ሕይወት ከዚህ ክስተት በኋላ እንዴት ተለወጠ?
    - ይህ ቤተሰብ የኋላኋላ ስለ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ወሬ ሲሰሙ ምን የሚያስቡ ይመስልሃል?

**አስደሳች ዜናዎች**

ከኢየሱስ አንደበት «አትፍራ እመን ብቻ» ማለት «ነገሩን ለእኔ ተወው እኔ እጠነቀቅለታለሁ» ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ አንድ ነገር ፈርቶ ነበር፤ እርሱም ከአባቱ መለየት ነው፡፡ በጣም ከመፍራቱ የተነሳ በጌቴሴማኒ የደም ላብ እስኪያልበው ድረስ ደረሰ፡፡ በዚህ መንገድ መፍራት የሚገባን ከእግዚአብሔር መለየት ሲከሰት ብቻ መሆኑን ያሳየናል፣ ያም ገሀነም ነው፡፡ በእርሱ በሚያምኑት ሕይወት ውስጥ ሁሉን ነገር ወደ በረከት መለወጥ ይችላል ይፈቅዳልም፡፡

# ጥናት 7. የሴትነት ክብሯን (ማንነቷን) ያጣች ሴት (ማር. 5:25-34)

*መሠረተ አሳብ*

በሙሴ ሕግ መሠረት አንዲት ሴት ደም በሚፈሳት ጊዜ በእምነት በኩል እንደረከሰች ተደርጋ ትቆጠራለች። በዚያ ሰሞን አንድም ሰው የእርሷ የሆነውን ማናቸውንም ነገር ወይም እሷን ራስዋን እንዲነካ አልተፈቀደም። በዚያ ሁኔታ ውስጥ ባለችበት ጊዜ ወደ ቤተመቅደስ መግባት ከቶ አይፈቀድላትም። (ዘሌ.15)

1. በጥቅሱ ውስጥ የተገለፀችው ሴት የ30 ወይም 40 ዓመት ዕድሜ ያላት እንደሆነችና ከአፍላ የወጣትነት ዕድሜዋ ጀምሮ ስትታመም እንደነበረች ገምት። ይህ በሽታ፣ ብታገባ በሕይወቷ ላይ ምን ዓይነት ጉዳት ያደርሳል? ባታገባስ?
    - ሳያቋርጥ የሚፈስ ደም በአካልዋ ላይ ምን ዓይነት ነገር ያስከትላል?
    - እንደዚያ ያለ በሽታ ሴቲቱ ስለራሷ ባላት አመለካከት ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ያስከትላል?
2. ይህች ሴት በወጣትነቷ ዕድሜ እንደዚህ ባለው በሽታ ስትያዝ ስለ እግዚአብሔር ምን እንዳሰበች ለመገመት ሞክር።
    - በዚህ የረጅም ዓመታት ሕመም ጊዜ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረ ግንኙነቷ ምን ያህል ተለዉጦ ይሆናል?
3. በቁጥር 26 ውስጥ ይህች ሴት በአንድ ወቅት ንብረት እንደነበራት ይናገራል። ንብረቱን ከየት እንዳገኘችና በምን አገልግሎት ላይ ሊውል ታቅዶ እንደነበረ ለመገመት ሞክር።
4. እንበል በዘመኑ የአዋላጅነት ሙያ የነበራቸው ሰዎች ጠንካራ ባለሙያዎች አልነበሩም። እንደዚህም ሆኖ ይህች ሴትዮ ገንዘብዋን ሁሉ እንደዚህ ላሉ ሐኪሞች ከፍላ ሕክምና ለማግኘ ት መፈለግዋና የጤንነቷ መመለስ ምን ያህል ጠቀሜታ አለው?
    - በዚህ ዓይነት ሕይወቷ ሴትዬዋ ስለ ሐኪሞችና ሊያድኑ ስለሚችሉ የዘመኗ ባለመድሃኒተኞች ምን እንደ ተሰማት አስብ (26)?
    - በኢየሱስና በሌሎች ባለ መድኃኒቶች መካከል ምን ዓይነት ልዩነት አለ?
5. በሌሎች ባለመድኃኒተኞች ተስፋ የቆረጠችው ሴትዮ የኢየሱስን ልብስ ብቻ በመንካት መዳን እንደምትችል እንዴት እርግጠኛ ለመሆን ቻለች (28)?
    - በዚህ ክፍል ውስጥ እንደተጠቀሰችው ሴትዩ ኢየሱስ እጅግ አስከፊ ለሆነ ችግርህ በቀላሉ መፍትሔ መስጠት እንደሚችል እርግጠኛ ነህ?
6. ሌሎች በሽተኞች እንዳደረጉት ይህች ሴትዮ ኢየሱስን ለምን እርዳታ አልጠየቀችም?
    - ሴትዬዋ የኢየሱስን ልብስ መንካት እንደ መዳኛ መንገድ አድርጋ ለምን መረጠች?
7. በዚያ ግፊያ መካከል አንድ ሰው የልብሱን ጫፍ በቀስታ እንደ ነካ ኢየሱስ እንዴት ሊያውቅ ቻለ?
    - ኢየሱስ ሴትዬዋን ሳያናግራት ወደ ቤትዋ እንዳትሄድ ለምን አልፈቀደላትም?
8. ኢየሱስ በቁጥር 30 ላይ ያለውን ጥያቄ ሲጠይቅ ሴትዮዋ ምን ተሰምቷታል ብለህ ታስባለህ?
    - ኢየሱስ ወደ እርስዋ ዞሮ ፊትዋን በተመለከተ ጊዜ ሴትዮዋ በኢየሱስ ዓይን ውስጥ ምን ተመለከተች? (32)
9. ሴትዮዋ አንዳች ቃል ለኢየሱስ መናገር አላሰበችም። ነገር ግን በመጨረሻ ላይ እውነቱን ሁሉ በመናገር አበቃች። በመጨረሻ ላይ የተናገረችው ነገር ምንድን ነው? (33)
    - ይህንን በሚያህል ብዙ ቃል ስለ ራስህ እውነትን ለኢየሱስ ተናግረህ ታውቃለህ? ያልተናገርክስ ከሆነ ለምን?
10. ቁጥር 34 በሁለት መንገድ ሊተረጎም ይችላል። «እምነትህ ፈወሰህ» ወይም «እምነትህ አዳነህ» በሚል ሊተረጎም ይችላል። ኢየሱስ ይህን የተለየ ቃል ለምን ለዚህች ሴትዮ መናገር ፈለገ?
    - ኢየሱስና ይህች ሴት በተመሳሳይ ዕድሜ ክልል ውስጥ ቢገኙም እንኳ ኢየሱስ «ልጄ ሆይ» ለምን ይላታል?

አስደሳች ዜናዎች፣

በግርፋቱና በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደሙ ምክኒያት ኢየሱስ ከሕገ ኦሪት አንፃር ልክ እንደ ሴትዮዋ ሁሉ እንደ እርኩስ ሆኖ ነበር። እርሱን የሚነካ ሁሉ ርኩስ ሆኖ ይታይም ነበር። እንግዲህ ኢየሱስ ይህችን ሴትዮ ለማዳን የከፈለው ዋጋ ይህ ነው ። አንተንም እንዲሁ።

## ጥናት 8. የራስ ቅል (ጭንቅላት)ን በሳህን ላይ ( ማር. 6:16-29)

*መሠረተ አሳብ*
በእርግጥ ሄሮድስ በዚያን ጊዜ ንጉሥ አልነበረም:: ዳሩ ግን በሮማውያን ፈቃድ ተሹሞ ከፓለስታይን (ፍልሰጤም) አንዱን ክፍል ይገዛ የነበር ሃገረገዢ ነበር:: ዮሴፈስ የተባለ ዕውቅ የአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ ስለ ሄሮድስ ጋብቻ ሲፅፍ በመፅሐፍ ቅዱስ ያለውን እውነት ይገልፃል:: በዚህ ክፍል እንደጠቀሰው ሁሉ የሄሮድያዳ ልጅ ስለ ነበረችው ወጣት ሴት ከመፃፉም በላይ የወጣቷ ሴት ስም ሶሎሜ እንደነበር ጨምሮ ጠቅሷል:: መጥምቁ ዮሐንስ በተያዘ ጊዜ ዕድሜው 30 ዓመት ገደማ ነበር::

1. ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት ለምን ለመቀማት እንደፈለገ የተለያዩ ምክንያቶችን አስብ፣ ግለፅ? (17-18)
    - ሄሮድያዳ ባልዋን ትታ ሄሮድስን ለማግባት ለምን እንደፈለገች የተለያዩ ምክንያቶችን ግለፅ::

2. በሄሮድስ ሕይወት የግል ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት አስጊ ሆኖ እያለ መጥመቁ ዮሐንስ ራሱን በዚህ ጉዳይ ውስጥ ለምን አስገባ?
    - አንድ ሰው ስለ ግል ኃጢአትህ ሊወቅስህ ቢመጣ ምን ትላለህ?
    - ባልዋ ካደረገው ክፉ ስራ ይልቅ ሄሮድያዳ ለምን ዮሐንስን ጠላችው (19-20)?

3. ዮሐንስ ወህኒ ቤት ውስጥ በሰንሰለት ታስሮ በሚቀመጥበት ጊዜ ምን የሚያሰላስል ይመስልሃል? (ዮሐንስ ሄሮድስን በመውቀሱ ተፀፅቶአል ብለህ ታስባለህ?)

4. ዮሐንስ እስረኛ ሆኖ እያለ ሄሮድስ ግን ለምን ይፈራው ነበር (20)?

    - ዮሐንስ የሄሮድስ እስረኛ ሆኖ እያለ ለምን አልፈራውም?
    - ከዮሐንስ ንግግር ውስጥ የሄሮድስን ስሜት የቀሰቀሰው ምን ነበር?

5. የሄሮድያዳ ልጅ በአስራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ነበረች:: እስከዚህ ዕድሜ ድረስ ምን ዓይነት ሕይወት ታሳልፍ እንደ ነበር ተናገር?
    - ይህ ታሪክ በእናትና ልጅ መሀል ስላለው ግንኙነት ምን ዓይነት ስሜት ይሰጣል (21-28)?
    - አብዛኛውን በእርስዋ ዕድሜ ውስጥ ያሉ ልጃገረዶች እንደሚጠይቁት ይህች ልጅ ልዩ ስጦታ ለምሳሌ ፈረስ፣ ጀልባ ወይም ለልደትዋ ቀን አዲስ ልብስ ወዘተ ለምን አልፈለገችም?

6. ሄሮድያዳና ሴት ልጅዋ ለምን የዮሐንስን ራስ ፈለጉ? ማስገደል ብቻ አይበቃም ነበር? ራሱን በከረጢት ወይም በማጥን ውስጥ ሳይሆን ለምን በሳህን ላይ ማድረግ አስፈለገ?
    - በዚህ ጥቅስ ስንት ነፍሰ-ገዳዮችን ታገኛለህ?
    - ይህ ክስተት በዚህች ልጃገረድ የወደፊት ሕይወት ላይ ምን ዓይነት ጉዳት የሚደርስ ይመስልሃል?

7. ቁጥር 26 ስለ ሄሮድስ ምን ይገልፃል?
    - ከብዙ የክፋት ሰራው ሁሉ ይልቅ ዮሐንስን መገደሉ በሄሮድስ ላይ ለምን ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል? (16)
8. በመጨረሻው የሕይወቱ ሰዓት ዮሐንስ ምን እንደ ተሰማው ታስባለህ?
    - በመሢሁ ፊት የሚሄድ መልዕክተኛ ለምን በዚህ ዓይነት ዕድል ሞተ?
9. የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለ መምህራቸው ዕጣ ፈንታ ምን ያስባሉ ብለህ ታስባለህ? (29)
    - የዮሐንስ ሕይወት በማለዳ የተቀጨ ይመስልሃል? ምክንያትህን ስጥ::
    - የዮሐንስን ሕይወት ከሄሮድስና ከሄሮድያዳ ሕይወት ጋር አመዛዝን?
    - ስለ ዮሐንስና የኢየሱስ ሕይወትና ሞት ምን ተመሳሳይ ነገር ታያለህ? ልይነቱስ?

10. ለዘመናችንና ለግላችን ከዚህ ምንባብ የምንማረው ዋና ሀሳብ ምንድነው ብለህ ታስባለህ?

# ጥናት 9. 25 000 ጥቅልል እንጀራዎችና 10 000 ዓሶች (ማር 6:30-44)

*መሠረተ አሳብ*

*ይህ ተአምራት የተፈፀመበትን ቦታ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን መሪው በካርታ ላይ ለማሳየት ይሞክር፡፡ በተጨማሪም ከባሕር አጠገብ በቤተሰይዳ አቅራቢያ (ቁ.45) እስከ ዋናው ከተማ እስከ ገሊላ ድረስ ስንት ኪሎ ሜትር እንደሆነ መሪው ለክቶ ያመልክት፡፡ በተለይ የኢየሱስና የደቀ መዛሙርቱ ወደዚህ ሥፍራ መምጣት መምጣት ለእረፍት መሆኑን ተገንዘቡ* (31-32) ፡፡

1. *አንድ ሰው ብዙ ጊዜ ሥራ በዝቶበት የመብላት ዕድል ባያገኝ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ያመጣበታል* (31)?
   - *ብዙ ሕዝብ ቀደም ብለው በኩሬው አጠገብ ሲጠባበቁ መኖራቸውን ደቀ መዛሙርቱ ባዩ ጊዜ ምን ተሰምቷቸዋል ብለህ ታስባለህ?* (32-33)
   - *ኢየሱስ የዕረፍት ጊዜው ሊያልቅበት ቢሆንም ለምን በሰዎቹ አልተበሳጨም* (34)?

2. *ኢየሱስ ማስተማሩን ሲጨርስ ጊዜው ከእኩለ ቀን አልፏል፡፡ በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ምን ተሰምቷቸዋል ብለህ ታስባለህ?*
   - *ከዚያ ቦታ ወደ ዋና ከተማው ወደ ገሊላ በእግር መሄድ ምን ያህል ሰዓት እንደሚፈጅ ግለፅ፡፡ በሕዝቡ መካከል እናቶችና ልጆች እንደነበሩ ልብ አድርግ፡፡*

3. *በዚያን ጊዜ አምስት ጥቅልል እንጀራና ሁለት ዓሣ የአንድ ሰው ምሳ ነው፡፡ እንደዚያ ያለ ምሳ በገንዘባችን ምን ያህል ብር ይሆናል?*
   - *ደቀ መዛሙርቱ* 25 000 *ጥቅልል እንጀራና* 10 000 *ዓሣዎች ለማግኘት በስንት መንደሮች ውስጥ መዞር እንደነበረባቸው ታስባለህ* (36)?

4. *በዚህ ዘመን እንደዚህ ያለ ለ*5000 *ሰዎች የሚሆን ምግብ ምን ያህል ገንዘብ ያስከፍላል?*
*200 ዲናር በዚያን ጊዜ የአንድ ሰው ዓመታዊ ገቢ 2/3ኛውን የህል ነበር፡፡ ደቀ መዛሙርቱ በቀጥታ ይህን ዋጋ የገለጹት ለምንድር ነው* (37)?

5. *ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ «እናንተ ራሳችሁ የሚበሉትን ስጡአቸው» ለምን አላቸው* (37)?
   - *ደቀ መዛሙርቱ ለኢየሱስ ጥያቄ ምን መልስ ሰጡ?*

6. *ኢየሱስ ያዘዛቸውን ለማድረግ ደቀ መዛሙርቱ ድፍረት ከየት አገኙ?*(39)
   - *ሕዝቡ በሣር ላይ በተቀመጡ ጊዜ አንዳች ምግብ እንደሚያገኙ ያመኑ መሆናቸውን ታስባለህ? እንደሚመገቡ ከገመቱ ምግቡ ከየት ይመጣል ብለው አስበዋል?* (40)
7. *ድንጋዮችን ወደ እንጀራ ከመለወጥ ይልቅ ለምን እንጀራዎቹ በ5000... እጥፍ እንዲበዙ አደረገ?* (41-42)
   - *ኢየሱስ በሚሠራው ተአምርና ጠንቋዮች በሚያደርጉት ተአምራቶች መካከል ምን ዓይነት ልዩነት አለ?*

8. *የዘመናችን ክርስቲያኖች የዚህን ዓለም ረሃብተኞችን ለመመገብ ለምን በይበልጥ ፈቃደኞች እንዳልሆኑ የተለያዩ ምክንያቶችን ግለፅ? (የዘመናችን ክርስቲያኖች በምን ምን ጉዳዮች ተጠምደዋል?)*

9. *ኢየሱስ አንተ የምትሰጠውን ትንሹን ስጦታ እንኳ በ* 5 000 *ጊዜ ሊያበዛ እንደሚችል ታምናለህ?*
   - *በእምነትና በተጨባጭ ነገር መካከል ምን ልዩነት አለ?*

*አስደሳች ዜናዎች፤*

*ኢየሱስ ይህን ተአምራት ካደረገ በኋላ «ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ» አለ፡፡ ማንም ከዚህ እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል፡፡ «ይህ እንጀራ ለዓለም ሕይወት የሚሰጠው ሥጋዬ ነው»* (ዮሐ. 6: 51) *ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞቱ እራሱ የቅዱስ ቁርባን እንጀራ ሆነ ፤ ይህም ለእኛ የዘላለም ሕይወት እንጀራ ሆነ ማለት ነው፡፡*

## ጥናት 10. ኤፍታ - ተከፈት ! (ማር. 7፡ 31-37)

*መሠረተ አሳብ*

በጥቅሱ ውስጥ የሚገኘው ሰውዬ በግልጽ ከህጻንነቱ ጀምሮ ዲዳ ነበር። መናገር ስላልለመደ በዚህም ምክንያት ከሰዎች ጋር ግንኙነት ለማደረግ አልቻለም። (በዚያን ዘመን ገና የምልክት ቋንቋ አልነበረም)። ኢሳያስ ከ700 ዓመታት በፊት ደንቆሮዎች እንዲሰሙና ዲዳዎች እንዲናገሩ መሚሁ ይህን ያደርጋል ብሎ ተንብዮ ነበር። (ኢሳ. 35፡ 5፣ 37)

1. በቀን ውስጥ ምን ዓይነት ድምጽ እንደምትሰማ ለአፍታ አስብ። አንዳች ነገር መስማት የማትችል ቢሆን ኖሮ በጣም የሚያስቸግርህ ነገር ምን ሊሆን ይችላል ብለህ ታስባለህ?

2. የዚህ ሰው የልጅነት ወቅት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምት። (ወላጆቹ ይህን ሕፃን ለማስተማር፣ ከጉዳት ለመጠበቅ፣ እንዲሠራ ለማደረግ ወዘተ... ምን ዓይነት መሣሪያ እንደነበራቸው አስብ።) ይህ ልጅ ከአቻዎቹ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ነበረው? ስለራሱስ የነበረው አመለካከት ምን ሊሆን ይችላል ብለህ ትገምታለህ?

3. ይህ መስማት የተሳነው ሰው ትልቅ ሰው ሆኖ ከአቻዎቹ ጋር ስለሚኖረው የዕለት ተዕለት ኑሮ አስብ።
   - ምናልባት ይህ ሰው ለጥቂት ጊዜያት ምኩራብንና ቤተ መቅደስን ጎብኝቶ ይሆናል። ስለማይታየው እግዚአብሔር ምን ያህል የተረዳ ይመስልሃል?

4. «ሰውዬውን ወደ ኢየሱስ ያመጡት ሰዎች የጀርባ ሀሳብ ምን ነበር? ምን ሊያስቡ እንደሚችሉ ለመገመት የተለያዩ አማራጮችን አስብ።
   - ዲዳውን ወደ ኢየሱስ ለማምጣት ረድተህ ቢሆን ኖሮ ወዴት እንደምትወስደውና ለምን እንደሆነ እንዴት ትገልፅለታለህ?
   - በሕዝቡ መካከል መሆን ለዚህ ሰውዬ ለምን ተጨማሪ ችግር ሆነበት?

5. የድዳው ሰውዬ ጓደኞች በጠየቁት መንገድ ኢየሱስ ለምን አልፈወሰውም(32-34)?
   - ሰውዬው ከማመፅና ከመቃወም ፈንታ ከማይታወቀው «ረቢ» (መምህር) ጋር ለመሆን ለምን ፈለገ (33)?

6. በቁጥር 33-34 ውስጥ ያለውን አራቱን የምልክት ቋንቋዎች ምን ያህል ተረድቷል ብለህ ታስባለህ? (ኢየሱስ ሰውዬውን ከመፈወሱ በፊት ወደ ሰማይ መመልከቱ ምን ዓይነት መልእክት ሊያስተላልፍለት ፈልጎ ነው? በረዥሙ የመተንፈሱ ጉዳይስ ምንድር ነው?)

7. ጸሐፊው ቅዱስ ማርቆስ በወንጌሉ ውስጥ ኢየሱስ ሲፈውስ የተጠቀመበትን ቃል በአረማይክ ቋንቋ ለምን መዘገበ? (34)
   - ኢየሱስ በዚህ ሰዓት በፊትህ ቆሞ ለዚህ ሰውዬ የተናገረውን «ኤፍታህ - ተከፈት» የሚለውን ቃል ለአንተም ይናገራል። ይህ ምን ማለት ነው? ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለህን ግንኙነት አስብ። (ይህን በልብህ ልትመልስ ትችላለህ።)

8. አብዛኛውን ጊዜ አንድ ሕፃን ጠቃሚ የሆኑትን የቋንቋ ቃላትን ለመማር ሶስት (3) ዓመታት ይወስድበታል። ይህ ሰውዬ በቅጽበት ያንን መረጃ እንዴት ሊያገኝ ቻለ?

9. እያንዳንዱ የኢየሱስ ተአምራት ስለ ሰማይ አንዳንድ ነገሮች ይነግረናል። በዚህ ክፍል ውስጥ በተፈፀመው ተዓምር አማካይነት ስለዚሁ ጉዳይ ምን እንማራለን?
10. ኢየሱስ እንዳይናገሩ ቢያስጠነቅቃቸውም እንኳ ሰዎቹ ስለ ተአምራቱ መናገሩን ለምን ቀጠሉ? (36)
    - የዘመናችን ክርስቲያኖች ለእኩዮቻቸው እንዲናገሩ ኢየሱስ የፈለገው ዜና ስለ ምን ነበር?
    - ለክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተዓምራቶችን በመገናኛ ብዙሃን ማስተዋወቅ ትርፋማ (ውጤታማ) የሚያደርጋት ይመስልሀል?

**አስደሳች ዜናዎች ፤**

በኢየሱስና አባቱ መካከል የነበረው ጥልቅ ግንኙነት ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ ለአፍታ ተቋረጠ። ኢየሱስ በእግዚአብሔርና በእኛ በኃጢአተኞች መካከል ግንኙነት ለመመሠረት የከፈለው ዋጋ ይህ ነው።

## ጥናት 11. ከራሱ ፈቃድ ውጪ የሆነ አንድ ዓይነ-ስውር ሰው (ማር. 8፡ 22-26)

*መሠረተ አሳብ*

ይህ ሰውዬ ቀድሞ ያይ ነበር:: ምክንያቱም ከወንጌሎቹ እንደምንረዳው ኢየሱስ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው አንድ ጊዜ ብቻ ፈውሷል (ዮሐ.9:32 ) :: ይህ ጥቅስ ለአንዴና ብቸኛ ጊዜ ኢየሱስ አንድ በብዙ ሁኔታ ውስጥ የነበረውን ሰው እንደፈወሰ ይነግረናል:: ኢየሱስ ከዚህ ድርጊት በፊት ስለ መንፈሳዊ ዕውርነት ተናገረ(18)::ይህ ተአምራት ስለ ተደረገበት ስለ ቤተሰይዳ ሕዝብ አለማመን ኢየሱስ ወቀሳ አሰምቷል(ማቴ.11፡ 21)::

1. ዓይነስውሩ ሰውዬ ከኢየሱስ ለምን አንዳች ነገር አልጠየቀም ?
    - የዚህ ሰውዬ ሕይወት እስከዚህች ቀን ደረስ እንዴት እንደነበረ አስብ?
    - ይህን ሰውዬ ደካማ እንዲሆን ያደረገው ነገር ምንድ ነው? የተለያዩ ምክንያቶችን አስብ፣
2. የዓይነ ስውሩ ወዳጆች ኢየሱስ ምን እንዲያደርግለት ፈለጉ (22)?
    - የዚህ ሰው ወዳጆች ጥያቄን ኢየሱስ እንዴት መለሰ?
    - አንተ፤ ዓይነስውሩን ሰው ወደ ኢየሱስ እንዳመጡት ወዳጆች ዓይነት ሰው ነህ ወይስ በይበልጥ እንደ ዐይነስውሩ ዓይነት ሰው ነህ?

3. ኢየሱስ ሰውዬውን ከመንደሩ ውጪ እንጂ ለምን በቤተሰይዳ ውስጥ ሊፈውሰው አልፈለገም?
    - አንድ እንግዳ ሰው አንተ የማታየው እጅህን እንደያዘ አስብ:: ይህ ሲሆን ምን ታደርጋለህ ? (ኢየሱስ እጁን ይዞ ከመንደር ውጪ የሚያወጣው ዓይነስውሩ ሰውዬ ተቃውሞ አለማሳየቱ ምንን ያሳያል?)

4. ኢየሱስ ለዓይነ ስውሩ ያደረጋቸው አራት ነገሮች ምንድር ናቸው?
    - ሰውዬውን ለመፈወስ እነዚህን ብዙ ነገሮች ማድረግ ለምን አስፈለገ? በሂደት የተከሰተው እንዲህ ዓይነቱ ፈውስና ከኢየሱስ ጋር ለመነጋገር ዕድል ማግኘቱ ለዓይነስውሩ ሰው ምን ማለት ነው? ምን ዓይነት ትርጉም አለው?

5. ኢየሱስ ዓይነስውሩን ከመንደር ውጪ ያስወጣው ከሕዝቡ ነፃ ሊሆን ነበር:: ከመንደሩ ከወጡ በኋላ በእነርሱ አካባቢ ሰዎች የነበሩ ይመስልሀል? ወይስ ሰውዬው ብዙ ሰዎችን እንዳየ ማሰቡ ተሳስቶ ነው?
    - ኢየሱስ ሁለት እጆቹን በሰውዬው ራስ ላይ ጭኖ አንዳች ነገር ያይ እንደሆነ መጠየቁን አስብ :: ለጥያቄው ትክክለኛ መልስ ምን መሆን ይገባ ነበር?
    - በሁለተኛው ፈውስ ደረጃ ኢየሱስ ይህን ጥያቄ ለምን አልደገመም?

6. ምናልባት የሰውዬው ወዳጆች በመንደር ውስጥ ይጠብቁት ይሆናል:: ከተፈወሰ በኋላ ሰውዬው ወደዚያ መንደር እንዲመለስ ኢየሱስ ለምን አልፈለገም? (ወደ መንደሩ ቢመለስ ምን ይከሰት ነበር?)
    - ከዓይኖቹ ሌላ ከዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ የተፈወሱ ሁኔታዎች (አካሎች) ምንድን ናቸው?
    - ኢየሱስ ለዚህ ሰውዬ ያለው የመጨረሻ ግብ ምንድን ነበር?
7. ይህ ጥቅስ ኢየሱስን በልባችን እንድናምነው ይጠይቀናል(18):: ኢየሱስ አሁን በአንተ ፊት ቆሞ «አንዳች ነገር ታያለህ?» ቢልህ ምን ትመልስለታለህ?
    - እሱን ልታየው እንድትችል ኢየሱስ የልብህን ዓይኖች ለመክፈት እንዴት ዓይነት መንገድ ነው የተጠቀመው?
8. ይህ ተዓምራት ስለ ሰማይ ምን ያስተምረናል?

አስደሳች ዜናዎች፤

የዚህ ሰው ዓይኖች መከፈት ጌታ ራሱ እንደመጣ የሚያመለክት ሰዎች በቀጥታ ፊቱን እንዲያዩ የሚያደርግ ምልክት ነው (ኢሳ. 35፡ 4-5)::

ኢየሱስ ከዕይታቸው ፊት ተሰውሮባቸው ነበርና ብዙ ሰዎች እነርሱ እግዚአብሔር እንደሆነ አላወቁትም ነበር:: ለደቀመዛሙርቶቹ ጭምር ኢየሱስን እንደማንነቱ ማየት ቀላል አልነበረም(18):: ይህ ሁኔታ (ማለትም ከላይ ያለው ታሪክ) የሚያሳየን ኢየሱስን አጥርተን እስክናየው ድረስ ስለእኛ ወደ ኋላ እንደማይል ነው (1ዮሐ. 3፡ 2)::

## ጥናት 12. የአንድን ሰው ሕይወት ማዳንና ማጥፋት (ማር. 8፡ 34- 38)

*መሠረተ አሳብ*

ኢየሱስ በዚህ የወንጌል መፅሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ «መስቀል» የሚለውን ቃል ይጠቀሳል:: ቃላቶቹ ተከታዮቹን ሳያናውጡ አልቀሩም:: ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ማንም ሊገምት እንደሚችለው መስቀል ማለት ትልቁ ሃፍረት ስለነበረ ነው:: የውርደቱ አንዱ ክፍል የተፈረደበት ሰው መንገድ ኃላፊዎች እንካ እያፌዙበት መስቀሉን ወደሚሰቀልበት ቦታ ተሸክሞ መሄድ ስላለበት ነው:: («ሕይወት» እና «ነፍስ» በጥንቱ የግሪክ ቋንቋ አንድ ቃል እንደነበሩ አስተውል) ::

1. ቁጥር 34-38
    - በዘመናችን ዋጋ ያለው ኑሮ የሚባለው ምን ዓይነት ሕይወት ነው? (በሌላ አነጋገር የራስን ሕይወት ማዳንና ማጥፋት ማለት በዘመናችን አተረጓጎም ምን ማለት ነው?
    - ኢየሱስ እነዚህን ቃላት ለማን ይናገራል?
    - ሰዎች ይህን ቃል ከመስማታቸው በፊት ኢየሱስን ስለ መከተል ምን ያስቡ ይሆን? ከሰሙ በኋላስ?
    - በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ኢየሱስን ለመከተል የሚፈቅድ ምን ዓይነት ሰው ይሆናል ብለህ ታስባለህ?
    - ኢየሱስ ብዙ ተከታዮችን ለማግኘት ከፈለገ እንዲህ ያለ ንግግር ለምን ይናገራል?

2. ቁጥር 34- ራስን መካድ

   በደቀ መዛሙርት ሕይወት ውስጥ ራስን መካድ ማለት ምን ዓይነት ትርጉም ይኖረዋል?
    - ባለህበት ሁኔታ ውስጥ ኢየሱስን ለመከተል ራስን መካድ ማለት ምን ዓይነት ትርጉም ይሰጥሃል?

3. ቁጥር 34- የገዛ ራስህን መስቀል መሸከም
    - ኢየሱስ ስለ «መስቀል» ሲናገር ምን ማለቱ እንደሆነ ታስባለህ? አንድ ዓይነት መከራ ብቻ ወይም በክርስትና እምነት ምክንያት የሚመጣ መከራ ይሆን?
    - ከመስቀል ውጪ ሕይወትህ ምን ዓይነት ይሆናል?
    - ኢየሱስ ተከታዮቹ ከመስቀል ውጪ የሆነ ሕይወት እንዲኖራቸው ለምን አልፈቀደም?
    - አንድ መከራ የሚቀበል ሰው መስቀሉን ከኢየሱስ እጅ ብቻ ቢቀበልና ከሰይጣን፣ ከሌላ ሰው ወይም በእድሉ አለመሆኑ ምን ልዩነት ይኖረዋል ?

4. ቁጥር 35- የገዛ ሕይወትን ማዳን ወይም ማጥፋት
    - ሰዎች በምን ዓይነት የተለያዩ መንገዶች ሕይወታቸውን ከመስቀል ዘወር ማድረግ ይፈልጋሉ?
    - ዋና ዓላማው መደሰት የሆነው ሰው፣ ደስተኛ የማይሆንበት ምክንያት ምንድን ነው?
    - የኢየሱስ ተከታዮች መስቀሉን ለመሸከም ኃይል ከየት ያገኛሉ?

5. ቁጥር 36-37 የገዛ ሕይወትን ማዳንና የገዛ ነፍስን ማጥፋት
    - ለምን ዓይነት ነገር ሰው ሕይወቱን ያጠፋል?
    - ኢየሱስ የሰውን ልጅ ነፍስ ለማዳን ምን ከፈለ?
6. ቁጥር 38- በኢየሱስና በቃሎቹ ማፈር
    - ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች መካከል ከፍ አርገህ ክርስቲያን ያልሆኑ ወዳጆችህ እየሰሙ መናገር የሚያስቸግርህ የትኞቹ ናቸው?
    - ኢየሱስ ራሱ በዚህ አመንዝራና ሀጢአተኛ ትውልድ መሀል ለእግዚአብሔር ቃል ለመዋጋት ድፍረቱ በሌላቸው ክርስቲያኖች የሚያፍረው ለምንድነው?
    - ኢየሱስ ባፈረበት ሰው ምን ይደርስበታል?

7. አስደሳች ዜናዎች - ጥያቄዎች
    - መስቀል ለሚሸከም አንድ ክርስቲያን ኢየሱስ አስቀድሞ በተመሳሳይ ጎዳና ላይ መስቀል ተሸክሞ መሄዱ ምን ትርጉም ይሰጠዋል?
    - ከነዚህ ሁኔታዎች በኋላ ኢየሱስ የራሱን ሕይወት/ነፍሰ ያጣል:: ለምን?

## ጥናት 13. ልበ መንታ አማኝ (ማር. 9፡14-29)

### መሠረተ አሳብ

አብዛኛውን ጊዜ ርኩስ መንፈስ ያለበት ሰው በርኩስ መንፈስ የተያዘ ሰው ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ ከአእምሮ በሽታ ወይም ከሚጥል በሽታ ወዘተ... የተለየ ነገር ነው፡፡ ክፉ መንፈስ በኢየሱስ የሚያምነውን ሰው ከቶ ሊይዝ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የተጠመቀ በኢየሱስ የሚያምን ስለሆነና መንፈስ ቅዱስ በልቡ ውስጥ ስፍራ ስለያዘ ነው፡፡ እንደ ሉቃስ አገላለጽ በዚህ ጥቅስ የሚገኘው ሕፃን ለወላጆቹ ብቸኛ ልጅ ነበር (ሉ.ቃ.9፡38) ፡፡

1. ልጁ በክፉ መንፈስ የተያዘበት አባት፤ የዕለትተዕለት ሕይወት ምን እንደሚመስል ገምት (17-18፡20-22)፡፡ (በወላጆችና በጎረቤቶች እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋረ ያለውን ግንኙነት ብሎም ልጁ እንዲፈወስ የሚደረጉትን ጥረቶች ወዘተ. . . ለማሰብ ሞክር) ፡፡
    - የልጁን ሕይወት ከጓደኞቹ ሕይወት ጋር አመሳክር፡፡
2. በቁጥር 14-18 በተገለፀው መሠረት የአባት ዋነኛው ችግር ምን ነበር? የልጁስ?
3. ሊታገሣቸው አስቸጋሪ ስለሆነው ስለማያምን ትውልድ ኢየሱስ ሲናገር ወደ ማን ያመለክታል? (19)
    - በተለይ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ስለማያምኑ ሰዎች ኢየሱስ ሊታገስ ከባድ የሆነበት ለምንድን ነው?
4. አባትየው ለእርዳታ በሚጮህበት ጊዜ « ዘንልን እርዳንም» ብሎ ለምን ራሱን በዚህ ጥያቄ (ልመና) ውስጥ ያካትታል?
5. በቁጥር 23 ውስጥ ኢየሱስ ከአባትየው የማይነዋወጥ እምነት የሚሻ ይመስላል፡፡ ለምን እንደዚያ አደረገ?
    - አንድ ሰው አንተ ቀድሞውኑ አዝነህ እያለህ ከአንተ ፍፁም እምነት የሚሻ ከሆነ ምን ይሰማሃል?
6. በቁጥር 24 ውስጥ አባት ባሰማው የጩኸት ቃላት ውስጥ ያመነውና የተጠራጠረው ነገር ምንድን ነው?
    - ለምትወደው ሰው ችግር እርዳታ ፍለጋ ወደ ኢየሱስ በጮኽ ጊዜ ያመንከውና የተጠራጠርከው ነገር ምን ነበር?
7. አባትዮው የሚያድን እምነት የነበረው መሆኑንና አለመሆኑን ከጩኸቱ ማረጋገጥ ይቻላል? ምክንያትህን ግለፅ፡፡
    - የልጁ አባት ኢየሱስን ያመነው መቼ ይሆናል ብለህ ታስባለህ? ሊሆኑ ይችላሉ የምትላቸውን የተለያዩ አማራጮች ዘርዝር፡፡
8. አባቱና ልጁ የማይነቃነቅ እምነት ባይኖራቸውም ኢየሱስ ይህን ቤተሰብ ለምን ረዳቸው?
    - ይህ ተአምር በማን እምነት ተደረገ (ተፈፀመ) ?
    - በችግር ውስጥ ላለው ለምትወደው ሰው እርዳታ ለማግኘት ምን ያህል እምነት ያስፈልጋል?
9. ልጁ ሕይወት እንደሌለው ሰው መሬት ላይ ሲተኛ አባቱ ምናልባት ሞቶአል ብሎ ያስብ ይሆናል፡፡ (26) በኢየሱስ ከመረዳቱ በፊት ያንን አስቸጋሪ ሁኔታ መለማመዱ ለምን አስፈለገ? (ቁ.25) ኢየሱስ ወዲያውኑ ቢረዳው ኖሮ ሳይማር የሚቀረው ነገር ምንድነው?
    - ኢየሱስ እኛን ከመርዳቱ በፊት በችግር ውስጥ እንድንዘፈቅ ለምን ይፈቅዳል? (ወዲያው እርዳታ ብታገኝ ሳትማር የምትቀረው ምንድን ነው?)
10. «ኢየሱስ እጁን ይዞ አስነሣና በእግሩ እንዲቆም አደረገው» (27)፡፡ የምታስብለትን የአንድ ሰው ስም በዚህ ዓረፍት ነገር ውስጥ አስገብተህ ቁጥር 27ን ስታነበው ምን ይነግርሃል?

### አስደሳች ዜናዎች

ክፉ ሰዎችና ክፉ መንፈስ ኢየሱስን ቢያስቸግሩም በማይነቃነቅ እምነት በሰማያዊ አባቱ ሀይልና ፍቅር ታመነ፡፡ በኢየሱስ ፍፁም እምነት ቢኖረን እኛም ከጥርጣሬአችን ባሻገር ለችግራችን ከእግዚአብሔር ዘንድ ዕርዳታ ለማግኘት እንችላለን፡፡

## ጥናት 14. የአሰናካይ ሰው ዕድል (ማር. 9: 42-50)

*መሠረተ አሳብ*

በቁጥር 42 ላይ ያለው የግሪክ ቃል «ስካንደላይዞ» ማለት ኃጢአት እንዲሠራ «ማሰናከል፣ መፈተን» አንድን ሰው እንዲወድቅ ማድረግ ማለት ነው። በዚህ ጥቅስ ውስጥ የሚገኘው የኢየሱስ ቃል ለዚህ ዘመን እጅግ ተስማሚ ነው። በዘመናችን ዜናዎች ብዙ ጊዜ የሚናገሩት በሕጻናት ላይ ስለሚደረግ የወሲብ ጥቃትና ይህንኑ መረጃ የሚያመርቱ እየተበራከቱ ስለመምጣታቸው ሲሆን ይህም በብዙ መቶ ሺ ለሚቆጠሩ ሕፃናትን ሕይወት ስለማጥፋቱ ነው። ኢየሱስ በዚህ ክፍል የሚናገረው እንደዚህ ላለ አስከፊ ነገር ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በተራ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ስላለው ፈተና ስለ አንተና እንደ እኔ ላሉት ሰዎች ሕይወት ጭምር ይናገራል።

1. በቁጥር 42 ውስጥ ኢየሱስ እንደሚናገረው ዓይነት ቅጣት የሚበየንበትና ስለዚሁ ሁኔታ የሚገልፅ የቅጣት ህግ በማንኛውም ሀገር በሕገ መንግሥት ውስጥ ተካትቶ አናገኝም። ከተራ ቅጣት ይልቅ የኢያሱስ ቅጣት የጠበቀ መሆኑ በምን ምክንያት ነው? (እንደ ኢየሱስ አባባል ሕፃንን የሚያሰናክል ሰው ለምን ለተገቢ ቀብር እንኳ የማይገባ ሆነ?)

2. እጆች አንድን ሰው ኃጢአት እንዲሠራ ሰለሚያሰናክሉበት መንገድ አንዳንድ ምሳሌዎችን ጥቀስ? (43)
    - እግሮች አንድን ሰው ኃጢአት እንዲሠራ እንዴት ሊያሰናክሉ ይችላሉ (43)? ዓይኖችስ እንዴት ሊያሰናክሉ ይችላሉ (47)?
    - ፈተና ሲገጥምህ ወዲያውኑ ትነቃበታለህ?

3. በአደጋ እጆችህን፣ እግሮችህንና ዓይኖችን ከማጣት ወይም ስትሞት በሲኦል ውስጥ ለዘላለም ከመጣል የትኛውን በይበልጥ ትፈራለህ?
    - ከነዚህ ውስጥ የአንዱ መሆን ግድ ቢሆንና በልጆችህና በምትወዳቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ ቢከሰት የትኛው በይበልጥ ያስፈራሃል?

4. ልክ ኢየሱስ በዚህ ክፍል እንደሚያደርገው (እንደሚናገረው) አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ቁሞ መስበክ ቢጀምር አድማጮቹ ምን ይሉ ይሆን?

5. ኢየሱስ እንደዚህ ያለ አስቸጋሪ ምክር ሲሰጥ ምን ማለቱ ነው (43-47)?
    - አንድ የምትወደው ልጅህ ወይም ወዳጅ ክፉ ዐመል ባለው ሰው የግብረስጋ ወንጀል ቢፈፀምበት ኢየሱስ በዚህ ቦታ ስላሰተማረው ትምህርት ምን ታስባለህ?
6. አንድ ከዝሙት ኃጢአት ጋር እየታገለ ለማሸነፍ ላልቻለ ሰው (ላልቻለች ሴት) ምን ዓይነት ምክር ትሰጣለህ?

7. አብያተ ክርስቲያናት ስለ ፈተና፣ ስለ ጅምላ ኃጢአትና ስለ ገሃነም ኢየሱስ እንደ ሰበከ መስበክ ቢያቆሙ ምን ይከሰታል? (ስለ እግዚአብሔር ያለን አሳብ እንዴት ይለወጣል? የሰዎቹ ጠባይ እንዴት ይለወጣል? ከኢየሱስ መስቀል ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ይኖረዋል?)

8. በዘመናችን ያሉ የልቅ የወሲብ መረጃ ስርጭት አምራቾችና ተጠቃሚዎች ትልቁ ስሕተታቸው ምንድን ነው?
    - እነዚህን በተናጠል እና ከሕዝብ ወይም ከቤተክርስቲያን ጋር በቅንጅት እንዴት ልንዋጋቸው እንችላለን?

9. እነዚህን የኢየሱስ ትዕዛዛት መከተል እንዳቃተን ከተገነዘብን ማድረግ የሚገባን ነገር ምንድነው?

### አስደሳች ዜናዎች

የኢየሱስ እጆችና እግሮች ለምን በሚስማር እንደተቸነከሩና በውስጥም በውጪም ድቅድቅ ጨለማ ከቦት እንደሞተ አሁን ለማየት ችለህ ይሆን?

## ጥናት 15. ኢየሱስና ልጆች (ማር. 10፡ 13-16)

*መሠረተ አሳብ*

በኢየሱስ ዘመን ወንዶች ልጆች የስምንት ቀን ዕድሜ ሲኖራቸው የእግዚአብሔር መንግስት ሕዝብ ይደረጉ ነበር። ሆኖም ልጆች በሕብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው ደረጃ በአጠቃላይ ዝቅተኛ ነበር። « ፔይስ» የሚለው የግሪክ ቃል በዚህ ምንባብ ውስጥ «ልጅ» ለማለት ያገለገለ ሲሆን በማንኛውም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን ልጆችና ትናንሽ ሕፃናትን ጭምር ያመለክታል።

1. የአንተን ልጆች ወይም ሌሎች ልጆችን ስትመለከት እነዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች መሆናቸውን ለማመን ይቀልሃል ወይስ ከባድ ነው? ለምን እንደሆነ ምክንያትህን ግለጽ?

2. እነዚህ እናቶች ኢየሱስ የሚናገረውን በወጉ ሊረዱና ሊገነዘቡ የማይችሉትን ልጆቻቸውን ወደ ኢየሱስ ለማምጣት ለምን እንደፈለጉ የተለያዩ ምክንያቶችን ግለፅ።
   - አንተ ራስህ ልጅህን ወደ ኢየሱስ ብታመጣ ለምን ምክንያት ታመጣለህ?
   - በዚህን ጊዜ የነበሩ አብዛኞች እናቶች እንደዛሬዎቹ እናቶች ሁሉ ለምን ልጆቻቸውን ወደ ኢየሱስ አላመጡም ነበር?

3. ልጆች ወደ ኢየሱስ በተወሰዱ ጊዜ ደቀ መዛሙርት ለምን አልተደሰቱም?
   - ይህ በወንጌሎች ውስጥ ኢየሱስ «ተቆጣ» ተብሎ የተነገረለት ብቸኛ ክፍል ነው። በዚህ ሁኔታ ኢየሱስን ያስቆጣው ነገር ምንድን ነበር?

4. በአሁኑ ጊዜ ልጆችን ወደ ኢየሱስ ማምጣት ማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ለማገናኘት (ለመንፈሳዊ ትምህርት) ማምጣት ማለት ነው። ክርስቲያን ወላጆች እንኳ ቢሆኑ ልጆቻቸው በመኖሪያ ቤታቸው፣ በእሑድ ትምህርት ቤት፣ በቤተክርስቲያን ግቢ ወዘተ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲሰሙ ለምን አያደርጉም?
   - ያንተን ልጅ ወይም የልጅ ልጅን ወይም ሌሎች ሕፃናት የኢየሱስን ቃል እንዲሰሙ የምታደርግበት ተጨባጭ መንገድ ወይም የምትወስዳቸው ቦታ ካለ አስብ።

5. ከአዋቂዎች ይልቅ ለሕፃናት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ለምን ቀላል ሆነ?

6. ሕፃን ከአዋቂ በተለየ መንገድ ስጦታን እንዴት ይቀበላል?
   - ሕፃን ትልቁን ስጦታ ማለት የኢየሱስ ወዳጅነትንና የኃጢአት ስርየትን እንዴት ይቀበላል? አዋቂ ሰውስ ይህን እንዴት ይቀበላል?

7. ለልጆች ብቻ ስለ ተገባው የእግዚአብሔር መንግስት አስብ። ይህ መንግስት ከዚህ ዓለም መንግሥት በምን ይለያል?
   - የጥናት ክፍላችን ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምን ያስተምረናል?

8. ኢየሱስ በሌላ ጊዜ «ጽድቃችሁ ከፈሪሳውያንና ከሕግ አስተማሪዎች ጽድቅ ካልበለጠ ከቶ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አትገቡም» (ማቴ. 5፡20) አለ። በዚህ ቦታ ግን ሕፃናት እንኳ ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንደሚገቡ ተስፋ ይሰጣል ታዲያ ይህን ተቃርኖ የሚመስል ነገር እንዴት ታስታርቃለህ?

9. ኢየሱስ በዚያች ጧት የባረካቸው ሕፃናት ከዓመታት በኋላ አዋቂዎች ሆነዋል። ምናልባት ከእነርሱ አንዳንዶች ጥሩ ሰዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ መልካም ሰዎች አልሆኑም ይሆናል። አንዳንዶች ደስተኞች ሆነዋል፣ ሌሎቹ ደግሞ ይህን ያህል ደስተኞች ላይሆኑ ይችላል። ከኢየሱስ የተቀበሉት በረከት ለእነርሱ ዘላቂ ትርጉም ይኖረዋል ብለህ ታስባለህ? እንዲህ ከሆነ ይዘቱ ምንድን ነው?
   - በሕፃናቱ እናቶች ሕይወት ውስጥ የኢየሱስ በረከት እያደረ ምን ትርጉም ይሰጣል? በተለይም ልጆቻቸው ብዙ የኑሮ ችግሮችን መጋፈጥ በማጀምሩበት ጊዜዎች?

*አስደሳች ዜናዎች*

ምናልባት እነዚህ ህፃናት እናቶች «ኢየሱስ አንድ ጊዜ የባረከውን ልጄን ፈጽሞ አይረሳውም» ብለው አስበው ይሆናል። ልጆችህን በተመለከተም አንተም እንዲሁ ልታምን ትችላለህ።

## ጥናት 16. የምድር ላይ መዝገብ (ማር. 10፡ 17- 27)

*መሠረተ አሳብ*

እንደ ማቴዎስ አገላለጽ ይህ ሰውዬ ወጣት ነበር (ማቴ.19:22)። እንደ ሉቃስ አገላለፅ ደግሞ በሕብረተሰቡ መካከል ከፍተኛ ደረጃ ነበረው(ሉቃ.18:18)። ይህ ወጣት የፖለቲካ ሰው በእርግጥ በሕይወቱ ተሳክቶለታል። ልብ አድርግ፡- በወቅቱ የእስራኤል ባሕል እንደዚህ የተከበረ ሰው በማንም ፊት አይንበረከክም ደግሞም አይሮጥም።

1. ይህ የተሳካለት ፖለቲከኛ ሰው በቁጥር 17 ለይ የተገለፀውን ያልተጠበቀ ባሕሪ እንዲያሳይ ያደረገው ነገር ምንድር ነው?
   - ይህ ሰው ኢየሱስ እግዚአብሔር እንደሆነ አላመነም። እንዲህስ ከሆነ የጥያቄውን መልስ እንደሚያውቅ ለምን ጠበቀ(17-18)?
2. ይህ ሰው በመላ ሕይወቱ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የተከተለ ቢሆንም ስለ የዘላለም ሕይወት ለምን ማረጋገጫ አልነበረውም?
   - ከሞትን በኋላ ምን እንደሚደርስብን እኛም ሁልጊዜ የማናውቅበት ምክንያት ምንድነው?
3. ብዙ ፖለቲከኞች በገንዘብና ሴቶች አካባቢ ትልቅ ፈተና አለባቸው። ይህ ሰው ግን ከእነዚህ ፈተናዎች እንዲያምልጥ ያደረገው ምክንያት ምንድር ይሆናል ብለህ ታስባለህ (19-20) ?
   - እንደ ኢየሱስ አባባል የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በሥራ፤ በአሳብና በቃል መከተል ይገባል የሚል ነው። ይህ ሰውዬ ያንን ያደረገ ይመስልሃል?
   - እነዚህን ትዕዛዛት መጠበቅህን በታማኝነት ለኢየሱስ ልትነግር ትችላለህ?

4. ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ይህ ሰው አሁንም አንድ ነገር ይጎድለዋል። ያ ነገር ምን ሊሆን ይችላል(21)?

5. አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች እንደ መዝገባቸው (ሀብታቸው) የሚቆጥሩት ምን ዓይነት ነገሮችን ነው (21)?
   - ይህ ወጣት ሰው ሁለት ዓይነት መዝገቦች በምድር ላይ ነበሩት። እነዚህ ምንድን ናቸው?
   - በሰማይ እንዴት መዝገብ መሰብሰብ እንችላለን?
   - የምድር መዝገብን ከሰማይ መዝገብ ጋር አመዛዝን። ልዩነታቸው ምንድን ነው?

6. ይህ ወጣት ሰውዬ ምናልባት ቤተሰብና የሚንከባከባቸው አዛውንት ወላጆች ይኖሩት ይሆናል። በቁጥር 21 የተገለፀውን የኢየሱስን ትዕዛዝ ቢከተል ኖሮ ምን ያጋጥማቸው ነበር?
   - በዚህ ወጣት ሰውዬ ሁኔታ ውስጥ ብትሆን እግዚአብሔር ለሚስትህ፣ ለልጆችህና ለወላጆችህ እንደሚጠነቀቅላቸው ልታምን ትችላለህ?
   - ኢየሱስ ንብረትህንና ቆጥበህ ያከማቸኸውን ገንዘብህን በመተው ብቻ ደቀ መዝሙሩ እንድትሆን ቢፈቅድልህ ምን ታደርጋለህ?

7. ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ኢየሱስ ይህን ሰውዬ ቢቀበለው ኖሮ ምን ይከሰት ነበር? በቁጥር 21 መሠረት ኢየሱስ ይህን ወጣት ሰው አይቶ ወደደው። እንዲህ ከሆነ ትቶት እንዲሄድ የሚያደርገውን ከባድ ነገር ለምን ነገረው?

8. ይህ ሰውዬ መዝገቡን (ሃብቱን) ለመተው እንደማይችል በተገነዘበ ጊዜ ሌላ ምን አማራጭ ነበረው?
   - ሰውዬው ከእግዚአብሔር ይልቅ ገንዘቡን እንደሚወድ ተናዞ ኢየሱስን ይቅርታ ቢጠይቀው ኢየሱስ ምን ያደርግ ነበር ብለህ ታስባለህ?
9. ኢየሱስ ለዚህ ሀብታም ወጣት ሰውና ለጴጥሮስ የሰጠውን መልስ አመዛዝን (27)። መልሶቹ ለምን በፍፁም የተለያዩ ሆኑ?
   - በምድራዊ መዝገብ (ሃብት) ፍቅር ልቡ የታሰረውን ሰው እንኳን እግዚአብሔር ሊያድን ይችል እንደሆነ ተወያዩ?

**አስደሳች ዜኛዎች**

ኢየሱስ ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ ሰማያዊ መዝገቡን ተወ! በምድራዊ ሃብትና ሌሎች ጣኦታት እንደ ታሠረ ዓይነት ሰው በመስቀል ላይ ተቀጣ ። ይህ ለምን እንደሆነ ታውቃለህ?

## ጥናት 17. ጠቅላይ ሚስቴር የሚሆን ማነው ? (ማር. 10፡ 32- 45)

*መሠረተ አሳብ*
*ያዕቆብና ዮሐንስ ሀብታም ዓሣ አጥማጅ የሆነው ዘብዴዎስ የሚባል የገሊላ ሰው ልጆች ነበሩ። እነርሱም ጴጥሮስን ጨምሮ ዋነኞቹ ደቀ መዛሙርት ነበሩ። ኢየሱስ አንድ ጊዜ ያዕቆብና ዮሐንስን የነጎድጓድ ልጆች ብሎ ጠርቷቸዋል። በዚህ ጊዜ ኢየሱስ መከራ ሊቀበልና ሊሞት ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በመንገድ ላይ ነበር። ኢየሱስ ከዚህ በፊት ስለ መሞቱ ሁለት ጊዜ ተናግሯል።*

1. *ያዕቆብና ዮሐንስ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ የነበረው ለምን መስሏቸው ነበር?*
   - *በቁጥር 33-34 የተጠቀሰውን የኢየሱስ ትንቢት እነዚህ ወንድማማቾች ለምን ትኩረት አልሰጡትም?*

2. *ያዕቆብና ዮሐንስ ቀድሞውኑ በኢየሱስ አምነዋል፤ ነገር ግን መከራ ሊቀበልና ሊሞት እንደሚገባው ገና አላመኑም። አንድ ሰው የኢየሱስን መሞት አስፈላጊነት በማያይበት ጊዜ ከጌታና ከክርስትና ሃይማኖት ምን ይጠብቃል?*

3. *ያዕቆብና ዮሐንስ የዘብዴዎስ ልጆች በኢየሱስ መንግሥት ውስጥ የካቢኔነት ወንበር ካገኙ በኋላ ምን ለማድረግ የሚፈልጉ ይመስልሃል?*
   - *በዓለማችን ውስጥ የሥልጣን ጥማት ለምን በጣም የተለመደ ሆነ?*
   - *ስልጣንህን ወይም ሀይልህን በቤተሰብህ ውስጥ ባሉት ሰዎች ላይ ወይም በሥራ ቦታ እንዴት ተጠቅመህበታል?*
4. *በመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ «ጽዋ» የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ መከራን ያመለክታል። ኢየሱስ በመስቀሉ ቀኝና ግራ እንዲሆኑ ቢፈቅድላቸው ኖሮ ወንድማማቾቹ ምን ይመልሱ ነበር (38-39)?*
   - *ሊሰጥህ ካለ ኃላፊነትና ሥልጣን አንዱ ክፍል መከራ እንደሆነ ብተውቅ ሃላፊነቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ነህ?*

5. *የያዕቆብና ዮሐንስ ኃጢአት*
   *(ሀ) ከኢየሱስ ጋር ባለው ግንኙነት እና*
   *(ለ) ከጎረቤቶች ጋር ባለው በኩል ምን ይመስል ነበር?*

6. *በዚህ ሁኔታ ውስጥ አስርቱ ደቀ መዛሙርት ለምን በዘብዴዎስ ልጆች ተናደዱ (41)?*
   - *ይህ የጥናት ክፍል በክርስቲያኖች መካከል ስላለው ጥል እንዲሁም ጥሎ እንዴት እንደሚከሰት ምን ያስተምረናል?*

7. *ኢየሱስ ለመሪዎች ያስቀመጠው ሃሳብ ምን ያህል ስር ነቀል የሆነ ሃሳብ ነው (42-44)?*
   - *ኢየሱስ በዚህ ሰፍራ ያስቀመጠው ቁልፍ የመሪነት ሃሳብ በዘመናችን ክርስቲያኖች ምን ያህል የተለመደ ነው ብለህ ታስባለህ?*
   - *በቁጥር 43- 44 ላይ የተጠቀሰውን የኢየሱስን ትምህርት ምን ያህል ተከትለሃል? (መልሱን በልብህ ውስጥ ልትመልስ ትችላለህ)*

8. *በኢየሱስ እና በወንድማማቾቹ (ያዕቆብና ዮሐንስ) መካከል ትልቁ ልዩነት ምንድነው?*
9. *ኢየሱስ የባርያን ሥራ እንዴትና መቼ ሠራ(45)? (መልሱ ከዚህ ጥቅስ ውጪ ይገኛል።)*
   *« ቤዛ » የሚለው ቃል ባርያ የተገዛበትና ነፃ የወጣበትን ዋጋ የሚያመለክት ነው። ቁጥር (45) እንደገና አንብብና ከራስህ ሕይወት ጋር አዛምድ። ኢየሱስ ከምን ገዝቶ ነፃ አወጣህ? በምን ዋጋ?*

*አስደሳች ዜናዎች፤*
*ኢየሱስ የፍቅር አገልግሎቱን ዘወትር ሊሰጥህ ይመኛል። እርሱ የኃጢአት ይቅርታ እንድትቀበል ይፈልጋል፤ የተሰጠህን ሥልጣን ያለ አግባብ የመጠቀምህን ኃጢአት ይቅርታ ጭምር ።*

**ጥናት 18. የዓይነ ስውሩ ለማኝ ጩኸት (ማር. 10፡ 46-52)**

***መሠረተ አሳብ***

*ታሪክ እንደሚነግረን፤ ኢየሱስ ኢያሪኮን አንድ ጊዜ ብቻ ነበር የጎበኘው ፡፡ ይኸውም የሆነው ወደ ኢየሩሳሌም ባደረገው የመጨረሻ ጉዞ ወቅት ነበር፡፡ የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ በቀጥታ ከዳዊት ትውልድ ሐረግ ነው፡፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለዳዊት ቃል እንደገባው ሁሉ ዘሩ በእስራኤል ዙፋን ላይ ለዘለዓለም ይቀመጣል (2ሳሙ.7፡2-4) ፡፡ በዘመኑ ሀገሪቷን ይገዙ የነበሩ ሮማዊያን ማንም ቢሆን ያለፉትን የእስራኤል ነገስታት እያነሳ ወይም እያመሳከተ ቢናገር ፈጽማው አይታገሱትም ነበር፡፡*

1. *ኑሮህን በልመና መግፋት ቢኖርብህ ኖሮ ላንተ ከባድ የሚሆነው ነገር ምን የሚሆን ይመስልሃል?*

2. *አንድ ሰው ከዓመት ወደ ዓመት በመንገድ ዳር ሲቀመጥ ምን ሊማር ይችላል?*
    - *ኢየሱስ በሶስት ዓመታት ውጤታማ የአገልግሎት ጊዜው ከኢያሪኮ (በርጤሜዎስ የሚኖርባት ከተማ) በስተቀር ሁሉንም የእስራኤል መንደሮች የጎበኛቸው መሆኑን በርጠሜዎስ ሲሰማ ምን ይሰማዋል ብለህ ታስባለህ?*

3. *በርጠሜዎስ ወደ ኢየሩሳሌም (ከኢያሪኮ 30 ኪ.ሜ. የምትርቅ ከተማ) ማለትም ኢየሱስ ወደ ሚገኝባትና ወደ ተመላለሰባት ቦታ ሄዶ ለመፈወስ ለምን አልፈለገም?*
    - *ኢየሱስ ወደ ኢያርኮ በመጣ ጊዜ በርጤሜዎስ ሊገናኘው እቅድ ይኖረዋል ብለህ ታስባለህ?*
    - *የዓይነ ስውሩ ለማኝ የማስታወስ ችሎታ (ብስለት) ምን ያህል ሊሆን ይችላል ብለህ ታስባለህ?*

4. *በርጠሜዎስ ኢየሱስ የንጉሥ ዳዊት ልጅ እንደሆነ እንዴት ተገነዘበ (47) ?*
    - *በርጠሜዎስ የዳዊት ልጅ ብሎ ድምፁን ከፍ አድርጎ በጮኸ ጊዜ ሮማውያንን ለምን አልፈራም?*
    - *ሰዎች ዝም ለማሰኘት በሞከሩ ጊዜ ጩኸቱ እንዴት ተለወጠ (47-48)?*
    - *የዳዊት ልጅ ተብሎ ስለተጠራበት ማዕረግና መጠሪያ ኢየሱሰ ምን ምላሽ ሰጠ?*

5. *በርጠሜዎስ ለእርዳታ ያደረገውን ጩኸት ሰዎች ዝም ለማሰኘት የሞከሩበትን የተለያዩት ምክንያቶች አስብ?*
    - *ይህንን ዓይነ ስውር ሰው ለዕርዳታ ሲጮህ በመገሠጽ ፈንታ የአካባቢው ሰዎች ምን ማደረግ ነበረባቸው? (48)*
    - *አንተ ለእርዳታ ስትጮኽ በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ሊሰሙህ ያልፈለጉበትን ጊዜ ታስታውሳለህ ? ለምን እንደሆነ ምን ታስባለህ?*

6. *ሰዎች ኢየሱስ እንደጠራው በነገሩት ጊዜ በርጠሜዎስ ምን እንደ ተሰማው ታስባለህ? (49- 50)*
    - *በርጠሜዎስ ምናልባት በጥንቃቄ ለሚይዛቸውና እንደብርድልብሰም፤ፍራሽና ሌላም ተግባራት የሚጠቀምባቸውን ጨርቆቹን በቅፅበት ለምን ወርውሮ ጣለ? (50)*

7. *ኢየሱስ በርጠሜዎስን ለምን እንደዚህ ያለ የተለመደ ጥያቄ ጠየቀው? (51)*
    - *ኢየሱስ ዛሬ ተመሳሳይ ጥያቄ ይጠይቅሃል(51)፤ የምትሰጠው ምላሽ ምንድነው?*

8. *ኢየሱስ የዚህን ሰውዬ ዓይኖች እንዴት ፈወሰ (52) ?*
    - *ቁጥር 52 በሁለት መንገድ ሊተረጎም ይቻላል፡- « እምነትህ ፈውሶሃል» ወይም «እምነትህ አድኖሃል » ኢየሱስ እነዚህን ቃላት በሰዎች ሁሉ ፊት ለምን ለበርጠሜዎስ ለመናገር ፈለገ?*

9. *በርጤሜዎስ ኢየሱስን በመንገድ ላይ ተከትሎታል ምናልባትም እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ ኢየሱስን ሳይከተል አልቀረም፡፡ ለምን ይህን ያደረገ ይመስልሃል?*
    - *በቀጣዩ ቀን ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ « የዳዊት ልጅ » ብሎ ሁሉም ሰው ይጮኽ ነበር (11:9-10)፡፡ በዚህ ጊዜ ለምን ሮማውያንን አልፈሩም ነበር?*
    - *በርጠሜዎስ ማየት በቻለበት በዚያው ሳምንት ባለውለታው የሆነ የተወደደ ሀኪሙ በመስቀል ላይ ተቸነከረ፡፡ የኢየሱስ መሞት ለበርጠሜዎስ ምን ትርጉም ይሰጠዋል ብለህ ታስባለህ?*

## ጥናት 19. የተረገመው ዛፍ (ማር. 11:12-14 እና 20-25)

*መሠረተ አሳብ*

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል የእግዚአብሔር ቁጣ ትዕዛዙን የማይጠብቁትን ሰዎች ያገኛቸዋል ( ዘዳ. 28: 15) :: አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ይህንን ቁጣ በድራማዊ ወይም ምሳሌያዊ ድርጊት አቅርበውታል:: የኢየሱስ ዛፉን መርገምም ይህንን መንገድ የተከተለ ነበር::

1. አንድ ሰው ሌላውን ሰው ቢረግም ምን ይከሰታል?
   - ከዚህ በፊት አንድ ሰው አንተን ረግሞ ከሆነ እንዴት እንደተመለከትከው ግለፅ::

2. ኢየሱስ ያለ ወቅቱ እንዴት ከበለስ ዛፍ ፍሬ ይጠብቅባታል?
   - ኢየሱስ ይህን ምሳሌያዊ ሥራ በሠራበት ጊዜ ዛፉ ማንን ወይም ምንን ያመለክት ነበር? (ኢየሱስ የራሱን ሕዝብ እስራኤልን የመርገሙ ትርጉም ምንን ያመለክታል ብለህ ታስባለህ ?)

3. ኢየሱስ ከራሱ ሕዝብ ምን ዓይነት ፍሬ ይጠብቅ ነበር?
   - ኢየሱስ ከራስህ ሕይወት የሚጠብቀው ፍሬ ምንድርነው?
   - ኢየሱስ ከቤተ ክርስቲያንህ ምን ፍሬ ይጠብቃል? ከአብያተክርስቲያናትስ?
4. ስለ ፀጋ ዘመን ምን እንማራለን? (የእግዚአብሔር የትዕግሥት ጊዜ) ምን ያህል ጊዜ ይቆያል?
   - የእግዚአብሔር ትዕግሥት ለአውሮጳና አሜሪካ አብያተ ክርስቲያናት መቼ የሚቋረጥ ይመስልሃል?

5. የተረገመ ሕይወት ምን ይመስላል? (ቁጥር 20-21)
   - የተረገመው በለስ ከኢየሱስ መስቀል ጋር ምን ተመሳሳይነት አለው?

6. ከዚህ በፊት በእምነት የሆነ ፀሎት ፀልየህ እንደሆነ የጠየከውን ነገር ስለማግኘትህ ተናገር (ቁጥር 22-24) ::
   - በተለምዶ ፀሎትና በእምነት ፀሎት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

7. አብዛኛውን ጊዜ ተራሮች ከዚህ ወደዚያ ቦታ እንዲንቀሳቀሱ ለምን አንጠይቅም?
   - በሕይወትህ ውስጥ « ተራራ » ተንቀሳቅሶ እንደ ሆነ እንዴት እንደተፈፀመ ተናገር::
   - ክርስቲያኖች «ተራሮች» እንዲወገዱ አዘው ሳይፈፀም ሲቀር ምን ታስባለህ?

8. አንድን ሰው ይቅር ለማለት አስቸጋሪው ነገር ምንድንነው (ቁጥር 25) ?
   - አንድን ሰው ይቅር ለማለት የማንችል ሲመስለን ምን ማድረግ አለብን?
   - ባልጀራውን ይቅር ለማለት የማይፈልግ ሰው ስለ ክርስትና እምነቱ ምን ያንፀባርቃል?

9. የበለስን ዛፍ ከመርገሙ በኋላ ኢየሱስ ያስተማረው ትምህርት ከመርገሙ ጋር እንዴት ይዛመዳል(22-25) ? (እንደ ትምህርቱ ከሆነ ኢየሱስ ከሕይወታችን የሚጠባበቀው ፍሬ ምንድን
   ነው?)
   - ኢየሱስ የሚያውቃቸውንና ሊገድሉት ሲያደቡበት የነበሩትን ጠላቶቹን እንዴት ይቅር ሊላቸው ይችላል?

*ማጠቃለያ*

- በሕይወቱ መጨረሻ ሳምንት ኢየሱስ ለምን የበለሱን ዛፍ ረገመ? ይህንስ ለምን አስቀድሞ አላደረገም?
- እንደምሳሌያዊ ወይም ወካይ ተግባር ኢያሱስ በለሱን ከረገመ በኋላ በቦታዋ ተተክቶ እርሱ ራሱ ርግማንን የመሸከሙን ትርጉም እንዴት ትመለከተዋለህ?

**አስደሳች ዜናዎች**

ጳውሎስ ከኢየሱስ ጋር የከበረ ልውውጥ እንደምናደርግና በመርገም ፈንታ በረከት እንደምናገኝ አሳይቶአል:: (ገላ. 3: 13- 14):: የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን መሪው ጥቅሱን ያንብብ::

## ጥናት 20. የሥጋ ትንሣዔ የለም (ማር. 12፡ 18-27)

*መሠረተ ሐሳብ*
ሰዱቃውያን በኢየሱስ ጊዜ ከነበሩት ሰዎች የተለዩ የዕምነት ወገን ነበሩ:: ሊቀ ካህናት አብዛኛውን ጊዜ ከእነርሱ መካከል የተመረጡ ነበሩ::( የሐዋ. 5፡7) ሰዱቃውያን በእግዚአብሔርና በአምስቱ የሙሴ የሕግ መጽሐፍት (ከዘፍጥረት-ዘዳግም) ያምናሉ:: ነገር ግን የሥጋ ትንሣኤ የመንፈስ ዓለም ወይም የዘላለም ሕይወት እንዳለ አያምኑም:: በእርግጥ የዘመናችን የልቅ አስተሳሰብ አራማጅ የስነ መለኮት ምሁራን በኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን ከነበሩት ሰዱቃውያን ጋር ይመሳሰላሉ (ቁጥር 24ን ተመልከቱ)::

1. ሰዱቃውያን ለጥያቄአቸው ኢየሱስ ምን እንዲመልስላቸው ይጠባበቁ ነበር (18-23)?
   - ሰዱቃውያን የሥጋ ትንሣዔ እንደማይቻልና አስቂኝ ነገር አድርገው ለምን ቆጠሩ?
   - በዚህ ምንባብ መሠረት ሰዱቃውያን ግድ የሚላቸው ዋና ነገር ምንድን ነው?

2. ቀጥሎ ያሉትን ሁኔታዎች አስብ::
   - አንተ ሰዱቃዊ ነህ እንበል እና ያንተ ወዳጅ መዳን በማይቻል ካንሰር በሽታ እንደተያዘ/ች ሰማህ፤ እንዴት ታፅናናዋለህ/ ታጽናናታለህ ?
   - አሁንም አንተ ሰዱቃዊ ነህ እንበል፤ እንዲት መበለት መጽናናት አቅቷት በምታለቅስበት ቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ብትገኝ ምን ትላታለህ?

3. በሥጋ ትንሣዔ የማያምን ሰው ስለ እግዚአብሔር ምን ዓይነት አስተሳሰብ አለው?
   - ስለ ዘላለማዊ ህይወት ወይም ገሀነም ለማያምን ሰው «ደህንነት» የሚለው ቃል ምን ትርጉም ይሰጠዋል?
   - ሰዱቃውያን ምን ዓይነት አዳኝ የሚጠባበቁ ይመስልሃል?

4. ሰዱቃውያን ከእውነተኛ ትምርትና ከሚያድን እምነት ለምን ይሸሻሉ (24)?
   - የዘመናችንየስነ መለኮት ምሁራን፤ ሰዱቃውያን እንዳደረጉት ተመሳሳይ ስህተት ለምን ያደርጋሉ?
   - ሰዎች የልቅ አስተሳሰብ አራማጅ የስህተት ትምህርት አሰተማሪዎች ሥጋዊ ትንሣዔን በሚያስክደው ትምህርት እንዳይታለሉ እንዴት ማስቆም ይቻላል?

5. ኢየሱስ በሙታን ትንሣዔ ያለውን እምነቱን ለመከላከል ምን ዓይነት መከራከሪያ ሃሳብ ተጠቀመ (26-27)?
   - የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን መሪው ስለ አብረሃም ስለ ይስሐቅና ስለ ያዕቆብ እምነት ከጥቅሱ ያንብብ (ዕብ. 11፡ 16-17) :: እነዚህ ሶስቱ የእምነት አባቶች በትንሣዔ የማያምኑ ከሆነ ስለ ሕይወታቸው ምን ዓይነት ድምዳሜ ለመስጠት ይገደዱ ነበር?
   - በሥጋ ትንሣዔ የማታምን ቢሆን ሕይወትህ ምን ይመስል ነበር?

6. በአዲስ ኪዳን መፅሐፍት ከፈሪሳውያን ጥቂቶቹ በኢየሱስ እንዳመኑ ነገር ግን ከሰዱቃውያን አንድም ሰው እንዳላመነ ይናገራል:: ይህ ለምን እንደሆነ ታስባለህ?

7. ይህ ክፍል ሞትን ለምንፈራ ሰዎች ምን መፅናኛ ይዞአል?
   - «እርሱ የሕያዋያን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም» (27):: የሚለው የኢየሱስ ቃል ለራስህ ምን ትርጉም ይሰጥሃል?

አሰደሳች ዜኛዎች
እግዚአብሔር የሕያዋን እንጂ የሙታን አምላክ ካልሆነ ለምን መሞት ተገባው? እኛን ኃጢአተኞችን ከዘላለም ሞት ወደ ለዘላለም ሕይወት ለማዳን ሌላ መንገድ ስላልነበር ነበር::

## *ጥናት 21. የኢየሱስ ዳግም ምጽአት (ማር. 13፡ 14-32)*

*መሠረተ አሳብ*

ኢየሱስ በዚህ ክፍል ውስጥ በአንድ ጊዜ ስለ ሁለት ድርጊቶች ይናገራል፡- የመጀመሪያው ኢየሱስ ከተሰቀለበት 40 ዓመታት በኋላ በ70 ዓ.ም አካባቢ ስለሆነው የኢየሩሳሌም መፍረስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቀጥታ ከዳግም ምፅአቱ በፊት ስላለው ዘመን (እኛ አሁን ስለምንኖርበት ጊዜ) ይናገራል፡፡

1. አንዳንድ ሳይንቲስቶች የሰው ልጅ ታሪክ የ24 ሰዓት ርዝማኔ እንዲኖረው ተደርጎ ቢመደብ የዓለም መጨረሻ ደግሞ እኩለ ሌሊት ላይ እንዲሆን ቢደረግ ኖሮ አሁን ጊዜው 23:55 (ለእኩለ ሌሊት 5 ደቂቃ ጉዳይ) ይሆን ነበር ይላሉ፡፡ ስለዚህ አሳብ ምን ታስባለህ? ምን አስተያየት አለህ?
   - አንተ በዓለም በሕይወት እያለህ ኢየሱስ ዳግም ቢመጣ ትወዳለህ? ምክንያቶችህን ስጥ?

2. «*ጥፋትን የሚያስከትል ርኩሰት*» (14)፡፡ ይህ በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ከክርስቶስ በፊት በ168 ዓ.ዓ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ ለግሪክ ጣኦት መሠውያ ወደ ሠራው ወደ ኤጳፋኒስ አንቲዮከስ ያመለክታል፡፡ በመጨሻው ዘመን እንዲህ ያለው ነገር እንደገና እንደሚከሰት ኢየሱስ ይተነብያል፡፡ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ጥፋትን የሚያስከትል ርኩሰት በመጨሻው ጊዜ ምን ዓይነት ነገር ይሆናል ብለህ ታስባለህ?

   - በ70 ዓ.ም ክርስቲያኖች የኢየሱስን ቃላት አስታውሰው ኢየሩሳሌም ስትከበብ ሸሽተው ለመዳን ችለዋል፡፡ በመጨሻው ዘመን እነዚህ ቃላት ምን ትርጉም ይሰጣሉ? ክርስቲያኖች ከምን መሸሽ ይገባቸዋል ( 14-18)?

3. በታላቁ መከራ ጊዜ የሰውን ዘር እንደ መቅሰፍት የሚመታው ምን እንደሆነ ኢየሱስ ለምን በግልጽ አልተናገረም (19-20) ?

4. በዚህ ጥቅስ መሠረት ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት በቤተክርሰቲያን የሚኖረው የሃይማኖት መልክ ምን ይመስላል (21-23) ? (በዚህ ጥቅስ እይታ ዓለምን የሚያዳርስ መንፈሳዊ መነቃቃት በመጨሻ ዘመን እንደሚሆን ስለሚያምኑት አንዳንድ ክርስቲያኖች ምን ዓይነት አስተያየት አለህ?)
   - እውነተኛውን ክርስቶስን የሚያውቁና የማያውቁትን እንዴት ልናውቅ እንችላለን ( 21-23) ?
   - የሐሰተኛው ክርስቶስ ነቢያት ምልክትና ተአምራት እንዴት ሊሠሩ ይችላሉ?
   - ምናልባት የሐሰተኛው ክርስቶስ ነቢያት ራሳቸው እውነተኞች እንደሆኑ ያምናሉ፤ እንደዚህ ክፉኛ እንዲስቱ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድን ነው?
   - በታላቁ መከራ ጊዜ እውነተኛ ክርስቲያን የሆኑት ሊታለሉ ይችላሉ? ምክንያቶች ስጥ?

5. በቁጥር 24- 25 በተገለጸው መሠረት ሰማይና ጠፈር እንዲለወጡ የሚያደርግ ምንድን ነው? የተለያዩ ምክንያቶችን አስብ፡፡

6. ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ በምርጦቹ ላይ ምን ይደርሳል? በሌሎቹስ ላይ (26-27)?

7. በበለስ ዛፍ በተናገረው ምሳሌ አማካይነት ኢየሱስ ዛሬ ምን ሊለን ይፈልጋል (28-29) ?

8. የልቅ አስተሳሰብ አራማጅ የስነ መለኮት ምሁራን ኢየሱስ ስለ ዳግም ምጽአቱ ሲተነብይ ተሳስቶአል ይላሉ (30) ፡፡ ስለዚህ ሀሳባቸው ምን ታስባለህ? (ኢየሱስ እንደ ሰብአዊ ፍጡር ሊሳሳት የሚችል ቢሆን ኖሮ የክርሰትና እምነት ዕጣ ፈንታ ምን ይሆን ነበር?)
   - ቁጥር (30) በእርግጥ ምን ማለት ነው ብለህ ታስባለህ?

9. በመጨሻው ዘመን ለሚኖሩ ምዕመናን የእግዚአብሔር ቃል ምን ትርጉም ይኖረዋል? (31)
   - ለግልህ ዛሬ የእግዚአብሔር ቃል ምን ትርጉም ይሰጥሃል?

10. የኢየሱስ ዳግም ምጽአት እስከ መጨረሻው ለምን ምስጢር ይሆናል (32)?

## ጥናት 22. ፍቅር ከቶ አይወድቅም (ማር. 14፡ 1-9)

*መሠረተ አሳብ*

ቀጥሎ የተጠቀሱት የንባብ ክፍሎች ስለ ቢታኒያዋ ማርያም ምን እንደሚያስተምሩ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን መሪው በአጭሩ ይናገር:- ሉቃስ 10፡ 38-42፤ዮሐንስ 11 እና 12፡ 1-11:: (ይህች ሴት በሉቃስ 7፡ 36-50 የተጠቀሰችው ሴት አይደለችም) የማርታ፣ የማርያምና አልዓዛር ወላጆች በእርግጥ ሞተዋል:: ምናልባት ላላገቡ ሴት ልጆቻቸው ለጥሎሽ ወይም ለኑሮ እንዲገለገሉበት ጥቂት ገንዘብ ትተውላቸው ይሆናል:: የኢየሱስ የመጨሻው ሳምንት ሕይወት አሁን ይጀምራል::

1. ወዳጅህ እንደሚሞት አስቀድመህ ብታውቅ ምን ዓይነት ስጦታ ትሰጠዋለህ?
   - ኢየሱስ በዚህ ስፍራ ስለ ራሱ ቀብር ይናገራል? (8) ማርያም ከደቀመዛሙርቶቹ በተለየ መልኩ ኢየሱስ በቅርብ ሊሞት እንዳለ የተገነዘበች ይመስልሃል? ምክንያቶችህን ግለፅ::

2. ከናርዶስ የተሠራውን ሽቱ መያዣ ብልቃጥ ለመግዛት አንድ ሰው በአማካይ በዓመት የሚያገኘውን ገቢ ያህል መክፈል አለበት:: ለዚህ ነው (ውድ ከመሆኑ የተነሳ) በአንድ ጊዜ አንድ ጠብታ ብቻ ሰው የሚገለገለው:: በእኛ ገንዘብ የብልቃጥ ዋጋ ምን ያህል ያወጣል?
   - ይህን ያህል ገንዘብ ለማጠራቀም ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?
   - ማርያም ይህን ብዙ ዋጋ የሚያወጣውን ሽቱ በገዛች ጊዜ ስለ ጥሎሽዋ ወይም ስለ መጦሪያዋ ምን አስባ ይሆን?

3. ማርያም ጥቂት ጠብታ ከመጨመር ፈንታ ለምን ብልቃጡን ሙሉ በኢየሱስ ራስ ላይ አፈሰሰች?
   - «መሢህ» እና «ክርስቶስ» የሚሉ ቃላት «የተቀባ» ማለት ናቸው:: የአይሁድ ነገሥታት አብዛኛውን ጊዜ በንግስናቸው ጅማሬ ላይ ይቀባሉ:: ኢየሱስ ለምን እስከ መቀበሩ ድረስ አልተቀባም ነበር?

4. ማርያም ገቢዋን ሁሉ ለናርዶስ ሽቱ መግዣ ጨረሰች:: ሆኖም በእርሰዋ ላይ ከቀረበው ወቀሳ (ትችት) ውስጥ የትኛው ነጥብ ይበልጥ ጎድቷት ይሆን (4-5)?

5. ኢየሱስ ስለ እርስዋ ሲሟገትላት የማርያምን ልብ ከወደቀበት ያነሳው ነገር ምን ነበር? (6-9)
   - ኢየሱስ የተናገራቸውን ቃላት ከገዛ ሕይወትህ ጋር ለማገናዘብ ትችላለህ:: እርስዋ «የሚቻላትን አደረገች» (8)
   - አንተስ ፤ ካሁን ጀምረህ ለኢየሱስ ምን ማድረግ ትችላለህ?

6. የማርያም ድርጊት ከኢየሱስ ድርጊት ጋር ምን ተመሳሳይነት አለው? (ማለት:- በመስቀል ላይ መሞቱ እንዲሁም በቁጥር 9 ላይ የተጠቀሰው « ወንጌል »... ወዘተ)
   - ከሁለቱ የትኛው የበለጠ «ማባከን» ነው ብለህ ታስባለህ?:- ማርያም ለኢየሱስ ያፈሰሰችው ዋጋው ውድ የሆነው ሽቱ፤ወይስ ኢየሱስ ለማርያም ሲል ኋላ ያፈሰሰው የከበረ ደሙ

7. ለዘላለም የሚታወስላት የማርያም የተለየ ባህሪ ምንድነው ብለህ ታስባለህ(9)?
   - አንተስ ምን ዓይነት መታሰቢያ ልታስቀር ታስባለህ (9)?

8. ማርያም ኋላ በዚያ ቀን ስለ ኢየሱስ ብላ «ስላባከነችው» ገንዘብ ምን ተሰምቶአት ይሆናል ብለህ ታስባለህ?
   - ማርያም ኢየሱስን ይህን ያህል መውደድ እንዴት ተማረች?
   - ማርያም እንደ ወደደችው እና እንዳደረገችው ኢየሱስን መውደድ እንዴት እንማራለን?

*አሰደሳች ዜናዎች*

ማርያም ኢየሱስን መውደድ የተማረችው እርሱን በመስማት ነበር:: በአስፈላጊውና ትክክለኛ ጊዜ እርሱን ለማገልገል የቻለችውም በዚያ ምክንያት ነበር:: ማርያም አስቀድማ በወንጌል አመነች እናም ያ እምነት ሁሉን ነገር ለጌታ ለመስጠት የልብዋን ፍላጎትዋን አነሣሣ :: በእርስዋም ምክንያት ነበር በምድር ላይ ለመጨረሻ ጊዜ በሄደበት ሁሉ መልካሙን የናርዶስን ሽታ ያዳረሰው::

## ጥናት 23. «የኢየሱስ ክስ» የተሰኘ የውሸት ሸንጎ ( ማር. 15፡1-15 )

*መሠረተ አሳብ*

*የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን መሪው ለዚህ ጥናት ሰዎችን በሁለት በሁለት ወይም በሶስት ሶስት ይመድብ፡፡እያንዳንዱ ቡድን ከክፍሉ በአንድ ወይም በሁለት ነጥቦች ላይ ይወያያል ከዚያም ከጥቅሱ ያገኙትን ለእርስ በርስ ያካፍላሉ፡፡*

### 1. ጴንጤናዊው (ፖኒተስ) ጲላጦስ

*ይህ ሮማዊ ባለሥልጣን በወቅቱ ዓለምን ይገዛ የነበረውን ወራሪውን የሮማ መንግሥት ወክሎ የይሁዳን ግዛት ከ26- 36 ዓ.ም ያሰተዳደር ነበር፡፡ ጲላጦስ በወቅቱ የሮማ ንጉሰ ለነበረውንጉሥ ጢቤሪዎስ ቄሳር በቀጥታ ተጠሪ ስለነበር ስለአይሁድ አመፅም ሆነ አመፀኞች ጉዳይ አንዳች ወሬ አልፎ ወደ ንገሡ እንዳይደርስ እጅግ ይጠነቀቅ ነበር፡፡ ስለዚህም ወንጀለኞችን በሞት የመቅጣትም ሆነ የሞትን ፍርድ ለመሻር ፍርድ ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር፡፡*

**ቁጥር1- 15**

- *ከዚህ ጥቅስ ስለ ጲላጦስ ጠባይ ምን ትገነዘባለህ ? (ለምሳሌ፡- ለሁኔታዎች የነበረውን አመለካከት)*
- *በቁጥር 12 እና 14 ያሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በፍርድ ወንበር ላይ ተቀምጦ ስለሚጠይቅ ዳኛ ምን ታስባለህ?*
- *ጲላጦስ ባለው ሥልጣን ሳይጠቀም ሌሎች ውሳኔ እንዲሰጡለት ለምን አደረገ?*
- *ጲላጦስ ስለ ኢየሱስ ምን እንደ ተሰማው ምን ታስባለህ ? (ኢየሱስን ሁለት ጊዜ ለምን «የአይሁድ ንጉስ »ብሎ ይጠራዋል(ቁጥር 9 እና 12 )?*
- *እነዚህን ሁለቱን ሰዎች አነፃጽር፡- የሮማውያን ገዢና የአይሁድ ንጉሥ፡- በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድንነው?*
- *በመጨረሻ ይህን ሕጋዊ ክስ ማን ወደ ፍፃሜ አመጣው?*
- *ጲላጦስ ኢየሱስን አስገርፎና እንዲሰቀል አሳልፎ በሰጠው ጊዜ ምን ተሰምቶታል ብለህ ታስባለህ (15)?*
- *ጲላጦስ ሕሊናውን ለማረጋጋት እንዴት ሞክሯል ብለህ ታስባለህ?*
- *በዚያን ጧት በጲላጦስ ቦታ ብትሆን ክሱን እንዴት አድርገህ ትይዘው (ታስፈፅመው) ነበር?*

### 2. በርባን

*ነፍሰ ገዳይና የፖለቲካ አመፅ መሪ ሲሆን የስሙ ፍቺ «የአባት ወንድ ልጅ» ማለት ነው፡፡*

**ቁጥር 6-15**

- *ይህ ሰው ምን ዓይነት የሕፃንነት፣ የወጣትነትና የአዋቂነት ጊዜ እንደነበረው ገምት፡፡ ምንአልባት ይህንን ሰው አመፀኛና ነፍስ ገዳይ ያደረገው ምንድን ነው ብለህ ታስባልህ?*
- *ያንተ አስተዳደግ ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ቢሆን ኖሮ፤ አንተ ራስህ ነፍሰ ገዳይ ትሆን ነበር? ለምን አልሆንክም? የምትሆንስ ከሆነ ለምን ትሆናለህ?*
- *ሞት ተፈርዶበት ወደ ሞቱ እየተጓዘ በበርባን አዕምሮ ውስጥ ምን ዓይነት አሳብ ይመላለስ ነበር ብለህ ታስባለህ?*
- *በርባን ከተፈታ በኋላ በእርሱ ፈንታ በመስቀል የተቸነከረውን የአንድ ሰው ሞት ለማየት ሄዶአል ብለህ ታስባለህ?*
- *ከኢየሱስ ጋር ባለን ግንኙነት አንፃር እኛ ሁላችን በምን ዓይነት ሁኔታ በርባንን እንመስላለን?*

## 3. የካህናት አለቃ

አብዛኛውን ጊዜ በአንድ በተወሰነ ወቅት አንድ ሊቀ ካህን ብቻ ነበር የሚኖረው:: ይህ ታሪክ በተፈፀመበት ወቅት ግን ግን ሁለት ሊቀካህናት ነበሩ:: እነርሱም ቀያፋ የተሰኘ የካህናት አለቃ (ከ18-36 ዓ.ም) እና የእርሱ አማች የነበረ ሃና ሲሆን ሃና ሥልጣኑን ከቀያፋ ቀድሞ የያዘ ነበር:: ሃናም ማድረግ የሚፈልገውን ተፅዕኖ ሁሉ በቀያፋ በኩል ያሰፈፅም ነበር::

ቁጥር 1-15

- የካህናት አለቆች በሕይወታቸው ውስጥ ትልቁ ጥሪ ምንድነው ይላሉ ብለህ ታስባለህ?
- የካህናት አለቆች ለምን በኢየሱስ ቀኑ ?
- የካህናት አለቆች በኢየሱስ ላይ ያነሳሳቸውን ድብቅ ውስጣዊ ሃሳብ ለምን አልተገነዘቡም?
- ከእነዚህ ከሁለቱ የባሰ ወንጀል የሆነው የቱ ነው ብለህ ታስባለህ? የካህናት አለቆች በሕግ ስም ያደረጉት የሞት ወንጀል ወይስ በርባን በአመጻው ጊዜ ያደረገው የነፍስ ማጥፋት ወነጀል?
- አጥባቂ ሃይማኖተኛ ሰው የዲያብሎስ መሣሪያ ሊሆን የሚችል ይመስልሃል?
- በአንዳንድ ሁኔታዎች ከሊቀ ካህናቱ አለቆች ጋር የምትመሣሰልበት መንገድ አለ? ካለ እንዴት ?

## 4. ሕዝቡ

ሕዝቡ ባለፈው እሁድ ለኢየሱስ «ሆሳዕና» ብለው ይጮኹ ነበር:: አሁን ግን ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ «ስቀለው» እያሉ ሲጮሁ እናያለን :: ከሕዝቡ መካከል በኢየሱስ ልዩ ልዩ ዕርዳታ የተደረገላቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ::

ቁጥር 8-15

- ሕዝቡ አደገኛው ነፍስ ገዳይ ነፃ እንዲወጣ ለምን ፈለገ?
- ሰዎች በጎ ነገር ባደረገላቸው ሰው ላይ እንዴት ዞሩ?
- ለኢየሱስ የሚሟገት አንድ ድምፅ እንኳ ለምን አልተገኘም? ወይሰ ለምን አንድ ድምጽ እንኳ ስለ ፍትሕ መጓደል ተቃውሞውን አላሰማም?
- በዚያች ጠዋት በሕዝቡ መካከል ብትገኝ ኑሮ ምን ታደርግ ነበር?
- በዚህ ጊዜ በአገራችን ውስጥ እንደዚህ ያለ ነገር ሊፈፀም ይችላል ብለህ ታስባለህ? ምክንያቶችን ግለጽ::
- ይህ ጥቅስ ስለ ድሞክራሲ መልካምና ክፉ ጎን ምን ያስተምረናል?

## 5. ኢየሱስ

ኢየሱስ በፍርድ ፊት ቀርቦ አንድ ዓረፍተ ነገር ብቻ ተናገረ (2):: ከዚያ ባሻገር ዝም ሲል እንመለከታለን::

ቁጥር 1-15

- እስከዚህ ጊዜ ድረስ «የሰው ልጅ» ከሚለው በስተቀር ስለራሱ ማንኛውንም ማዕረግ ኢየሱስ አልተቀበለም ነበር:: አሁን ለምን በይፋ የአይሁድ ንጉሥ እንደሆነ ተቀበለ ( 2)?
- በፍርድ ወንበር ፊት ኢየሱስ ለምን ራሱን አልተከላከለም?
- ኢየሱስንና በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን ሌሎችን ሰዎች አመሳክር:: ኢየሱስ ከነርሱ በምን ይለያል? (ኢየሱስን አስደናቂ የሚያደርገው በተለይ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምንድር ነው?)
- ኢየሱስ በአካባቢው ስለ ነበሩ ሰዎች ምን ተሰምቶታል ብለህ ታስባለህ?
- በምርመራው ጊዜ የኢየሱስን ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠው ማነው?(ጲላጦስ፣ እግዚአብሔር ወይስ ሰይጣን)?

## ጥናት 24. ማመን የማይቻል ትንሣኤ (ማር. 16፡ 1-14)

*መሠረተ አሳብ*

እንደ አንዳንድ የጥንት ታሪክ፤ ማርቆስ የጴጥሮስ አስተርጓሚ ነበር፡፡ ማርቆስ የጻፈውም ወንጌል በጴጥሮስ ዓይን የታየ የኢየሱስ ሕይወት ነበር፡፡ ከዚህ ወንጌል ውስጥ አንዱ ርእስ «የደቀ መዛሙርት እምነት ማጣት» የሚል ነው፡፡ ኢየሱስ ስለ ሞቱና ትንሣኤው አስቀድሞ ቢነግራቸውም ደቀ መዛሙርት ግን ይሆናል ብለው አላመኑም ነበር፡፡ ኢየሱስ በሞተ ዕለት ሥጋው ሽቱና ቅባት ተቀብቶ እንደነበረ ልብ አድርግ፡፡

1. ድንጋዩና መቃብሩን የሚጠብቁት ወታደሮች (1-3) እያሉ የገሊላ ሴቶች መቃብሩን ለመጎበኘት ለምን ቁርጥ ውሳኔ አደረጉ?

2. ከሁለት ቀን በፊት የተቀባው ሽቱ ተቀብቶ የተቀበረው ያለአግባብ ያልተያዘውን የኢየሱስን ስጋ በዓይናቸው አይተው የነበሩት ሴቶች አሁን ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ ሊቀቡት ለምን እንደፈለጉ ምን ታስባለህ?
   - በዚያ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ያለውን የወዳጅህን ሥጋ ለማየትና ለመንካት ትፈልጋለህ?
   - ዮሐንስ ብቻ ስለ ኢየሱስ ሞት መስክሯል፡፡ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት አንድ ጊዜ እንኳን የኢየሱስን ሥጋ ለማየት አልፈለጉም፡፡ ለምን ? ( በዚህ ሁኔታ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት ያለ ይመስልሃል? እንዲህ ከሆነ ምንድን ነው?)

3. በኢየሱስ ትንቢት መሠረት ሴቶቹ የኢየሱስን ትንሣኤ አምነው ተቀብለው ከሆነ እሁድ ጧት ወደ መቃብሩ ሲሄዱ ስሜታቸው ምን እንደ ነበረ ታስባለህ?

4. የመልአኩን ቃል በሰሙ ጊዜ ሴቶቹ ምን አሰቡ?(6)
   - መልአክ እንኳ ቢናገራቸውም ትንሣዓዉኑ ለማንም አለመናገራቸው ሴቶቹ እጅግ ፈርተው እንደነበር ያሳያል (8)፡፡ ለመሆኑ ይህን ያህል ያስፈራቸው ምን ነበር?

5. በአይሁድ ባህል የሴቶች ምስክርነት በፍርድ ወንበር ፊት እንደ በቂ አይወሰድም፤ ታዲያ ኢየሱስ የመጀመሪያ የትንሣዔው ምስክሮች እንዲሆኑ ሴቶችን ለምን መረጠ (7-10)?

6. ስለ ኢየሱስ ትንሣዔ የነበራቸው እምነት በእነዚህ ሴቶች ልብ ውስጥ መቼ እና እንዴት ተፈጠረ?

7. ሬሳን ከሞት እንደማንሳት ያህል የማይቻል የሚመስል በሕይወትህ ውስጥ አስቸጋሪ ነገር አለ? (ይህን በልብህ መመለስ ትችላለህ፡፡)
   - ኢየሱስ ስለ እምነት ማጣት ደቀ መዛሙርቱን እንደ ገሠፀ (14) አንተን ቢገሥጽህ ምን ትመልስለታለህ?

8. *በስጋ ትንሳኤ* (በክርስትና እምነት ውስጥ ብቻ በሚሰጠው ትምህርት) እና *ነፍስ አትሞትም* ( በብዙ ሐይማኖቶች የጋራ ትምህርት በሆነው ) በሚሉት መሀል ምን ዓይነት ልዩነት አለ?

9. እንደ ሥጋ ትንሣዔ ያለ ነገር ባይኖር ኖሮ ክርስትና ለሰው ልጅ ምን የሚያበረክተው ነገር ይኖረው ነበር?
   - አንድ ሰው የክርስትና ትምህርቶችን ሁሉ ያምናል እንበል፡፡ ነገር ግን የሥጋ ትንሣዔን አያምንም፡፡ ይህን ሰው ክርሲቲያን ነው ብለን መጥራት ለምን ያስቸግረናል?

10. ከሁለት ቀን በፊት ጴጥሮስ ጌታውን ካደ ወዲያውም ኢየሱስ የተለየ ሰላምታ ላከለት፤ ይህ ለጴጥሮስ
    ምን ትርጉም ይሰጠዋል? (7)
    - እጅግ ከባድ ኃጢአት እንደሠራህ ገምት፡፡ በዚያው ወቅት ኢየሱስ ሊያይህ እንደሚፈልግ መልእክት ቢልክልህ ምን ይሰማሃል?

ማውጫ


| ተ.ቁ | ርዕስ | ጥቅስ |
|---|---|---|
| 1. | የአስደሳች ዜናዎች ጅማሬ | 1: 1-11 |
| 2. | ጤናማ ነፍስ በጤናማ ሰው ውስጥ | 2: 1-12 |
| 3. | ለኢየሱስ መሰናከያ ተደረገ | 3: 1-6 |
| 4. | በማዕበሉ መካከል | 4: 35-41 |
| 5. | ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ | 5: 1-20 |
| 6. | አስከፊ የሆነ ነገር ሲከሰት | 5: 21-43 |
| 7. | የሴትነት ማንነቷን ያጣች ሴት | 5: 25-34 |
| 8. | ራስን በሳህን ላይ | 6: 16-29 |
| 9. | 25 000 ጥቅልል  እንጀራና 10 000 ዓሣዎች | 6: 30-44 |
| 10. | ኤፋታ ተከፈት | 7: 31-37 |
| 11. | ከፈቃዱ ውጪ የሆነ አይነስውር ሰው | 8: 22- 26 |
| 12. | የአንድን ሰው ሕይወት ማዳንና ማጥፋት | 8 34-38 |
| 13. | ልበ መንታ አማኝ | 9: 14-29 |
| 14. | የአሰናካይ ሰው ዕድል | 9: 42-50 |
| 15. | ኢየሱስና ሕፃናት | 10: 13- 16 |
| 16. | የምድር ላይ መዝገብ | 10: 17-27 |
| 17. | ጠቅላይ ሚኒስቴር የሚሆን ማነው? | 10:32-45 |
| 18. | የዓይነ ስውሩ ለማኝ ጩኸት | 10:46-52 |
| 19. | የተረገመ ዛፍ | 11: 12-25 |
| 20. | የሥጋ ትንሣዔ የለም | 11:18-27 |
| 21. | የኢየሱስ ዳግም ምፅአት | 13:14-32 |
| 22. | ፍቅር ከቶ አይወድቅም | 14: 1-9 |
| 23. | «የኢየሱስ ክስ» የተሰኘ የውሸት ሸንጎ | 15: 1-15 |
| 24. | ሊታመን የማይቻል ትንሣዔ | 16: 1-11 |